# አዲስ ዘመን

እፕድ

ማክሰኞ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 066 ኅዳር 6 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


# ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ያመጠቀቻት ሳተላይት ተልዕኮዋን አሳካታለች




**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ያመጠቀቻት ETRSS-1 የመሬት ምልከታ ሳተላይት ተልዕኮዋን በአግባቡ ማሳካት መቻሏን የስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት አስታወቀ። ሳተላይቷ ከታቀደላት ጊዜ በላይ አገልግሎት እየሰጠች ነው።

የስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ አብዲሳ ይልማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ኢትዮጵያ የመሬት ምልከታ ሳተላይት ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር ማምጠቅ የቻለች ሲሆን፤ ተጠቃሽ የሆነችው ETRSS-1 የመሬት ምልከታ ሳተላይት ከመጠቀችበት ታኅሣሥ 10 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ተልዕኮዋን በአግባቡ ማሳካት ችላለች። ሳተላይቷ በዋናነት የመሬት ምልከታ ሥራዎችን ስትሠራ ቆይታለች።

እንደ አቶ አብዲሳ ገለጻ፤ መጀመሪያ ዲዛይን ሲደረግ ሳተላይቷ ለሁለት ዓመት ተኩል እንደምታገለግል ተደርጎ የታቀደ ሲሆን፤ አሁን ላይ ከታቀደላት ጊዜ በላይ ተጨማሪ አምስት ወራትን አገልግላለች። ከመጠቀች አሁን ላይ ወደ ሁለት ዓመት ከ11 ወራት ሆኗታል። ሳተላይቷ ምንም ሳትሆን ከታቀደላት ጊዜ በላይ እንድታገለግል ማድረግ የተቻለው ከእንጦጦ ማዕከል ያልተቋረጠ የቁጥጥርና የክትትል ሥራ በአግባቡ በመከናወኑ ነው።

የመሬት ምልከታ ሳተላይት በመሬት ዙሪያ እየተሽከረከሩ ፎቶግራፎችን በማንሳት የመላክ ሚና እንዳላቸው የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፤ ETRSS-1 የመሬት ምልከታ ሳተላይትም በግብርና፣ በተፈጥሮ ሀብት መስክና ከመሬት አስተዳደር ጋር የተገናኙ ሥራዎችን ለማከናወን ውጤታማ የሆኑ መረጃዎችን መስጠቷን አስታውቀዋል።

የሳተላይቷን መረጃ በመጠቀም የለሙና አሁንም ሆነ በቀጣይ ጥቅም ሊሰጡ የሚችሉ የተለያዩ ሞዴሎች እንዳሉ ጠቅሰዋል። በግብርናው ዘርፍ የሰብል ምርታማነትን በተመለከተ ከሳተላይቷ የተገኘውን መረጃ በመጠቀም ማልማት እንደተቻለም ጠቁመዋል። የደቡብ ምዕራብ

ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




pepsi





ፎቶ - እዩብ ተፈራ

ያስሚን ወሃቢረቢ

# ተሰርዞ የነበረው የጋራ መኖሪያ ቤቶች የዕጣ አወጣጥ ሥነሥርዓት ዛሬ ይከናወናል

## - 146 ሺ 892 ቆጣቢዎች ዕጣ ውስጥ ተካተዋል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ባጋጠመ ችግር ምክንያት ተሰርዞ የነበረው የጋራ መኖሪያ ቤቶች የዕጣ አወጣጥ ሥነሥርዓት ዛሬ እንደሚከናወን የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ቢሮ አስታወቀ። 146 ሺ 892 ቆጣቢዎች ዕጣ

ተሰርዞ የነበረው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# «በጦርነቱ የቆሰሉ አዕምሮዎች መታከም አለባቸው»

**- አቶ ኤርሚያስ ኪሮስ የስነልቦና ባለሞያ**

**ምሕረት ሞገስ**

አዲስ አበባ፡- ጦርነቱ የብዙ ሰዎችን አዕምሮ የጎዳ እና አጠቃላይ ሕይወታቸውን ያዛባ በመሆኑ በጦርነቱ የቆሰሉ የወገኖቻችን አዕምሮዎች መታከም እንዳለባቸው የስነልቦና ባለሙያው አቶ ኤርሚያስ ኪሮስ ተናገሩ።

በሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነቱ በተካሄደባቸው አካባቢዎች ተገኝተው የስነልቦና ህክምና ሲሰጡ የቆዩት የስነልቦና ባለሙያው አቶ ኤርሚያስ ኪሮስ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት፤ ጦርነቱ ብዙዎች የመኖር ትርጉም እንዲጠፋባቸው አድርጓል። ጥቂት የማይባሉ ሰዎች ጤናማ አስተሳሰባቸውን አጥተዋል። አሁንም በመጥፎ ትዝታ ውስጥ ናቸው። ብዙ ሰዎች ዓይናቸውን ሲከድኑ አስከሬን ሊመለከቱ ይችላሉ። ለመተኛት ሲያስቡ የሚረብሻቸው ድምፅ ይኖራል። ዛሬም ያኔ ከሰሙት ድምፅ ማምለጥ አልቻሉም።

«በጦርነቱ የቆሰሉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# ስለሰላም ስምምነቱ ተግባራዊነት ሁሉም አካላት አወንታዊ ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል

ገጽ 4






BIIROO KOMINIKEESHINII OROMIYAA

ኦሮሚያ ኮሚኒኬሽን ቢሮ

OROMIA COMMUNICATION BUREAU

## ክልሉ ሁሉም የመንግሥት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ አሳሰበ

ገጽ 3

# ክልሉ 17ኛውን የብሔር ብሔረሰቦች በዓል ለማክበር ተዘጋጅቷል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በአገር አቀፍ ደረጃ ለ17ኛ ጊዜ የሚከበረውን የብሔር ብሔረሰቦች በዓል በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ለማክበር መዘጋጀቱን የአማራ ክልል ምክር ቤት አስታውቋል።

የአማራ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ወይዘሮ ፋንቱ ተስፋዬ በዓሉን በማስመልከት ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ በዓሉ «ሕብረ ብሔራዊ አንድነት ለዘላቂ ሠላም» በሚል መሪ ቃል በአገር አቀፍ ደረጃ በሲዳማ ክልል አዘጋጅነት ኅዳር 29 ቀን 2015 ዓ.ም ለ17ኛ ጊዜ ይከበራል። አማራ ክልልም በዓሉን ከኅዳር 10 ጀምሮ በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ለማክበር ተዘጋጅቷል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት በዓሉ በተሟላ መልኩ እንዳልተከበረ አስታውሰው፤ አሁን ላይ የተፈረመው የሰላም ስምምነት ለአገራችን ሕዝቦች ትልቅ ፋይዳ ያለው በመሆኑ የክልሉ ምክር ቤት እና የክልሉ መንግሥት የሰላም ስምምነቱ ተግባራዊ እንዲሆን የድርሻቸውን ይወጣሉ ብለዋል።

በበዓሉ የክልሉን ሕዝብ የሚወክሉ እና የሚገልጹ ልዩ ልዩ የባህል ዝግጅቶችን የሚያቀርቡ የባህል ቡድን አባላት ከሁሉም የክልሉ አካባቢዎች ዝግጅት እያደረጉ መሆኑን ገልጸዋል።

ይህንንም የሚያስፈጽሙ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ተዋቅረው የቅድመ ዝግጅት ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት አፈ ጉባኤዋ፤ ከኅዳር 10 እስከ ኅዳር 25 ድረስ በክልሉ በሁሉም አካባቢዎች በፓናል ውይይትና በልዩ ልዩ ዝግጅቶች እንደሚከበር ገልጸዋል።



ወይዘሮ ፋንቱ ተስፋዬ

አፈጉባኤዋ እንደገለፁት፤ ከአጎራባች ክልሎች ወረዳዎች ጋር የሕዝብ ለሕዝብ ትስስር ሊፈጥሩ የሚችሉ መድረኮችም ይካሄዳሉ። የበዓሉን ቅድመ ዝግጅት ከወዲሁ በማጠናቀቅ ከኅዳር 10 እስከ 25 ቀን 2015 ዓ.ም በክልሉ በሁሉም አካባቢዎች የታቀዱት ተግባራት እንደሚፈጸሙ አስረድተዋል። በትምህርት ቤቶች ግን በዓሉ በዕለቱ ብቻ የሚከበር እንደሆነ አፈጉባዔዋ አስገንዝበዋል።

በዓሉ በ1ኛ እና በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም የኢትዮጵያን አንድነት በሚያጎሉ ልዩ ልዩ ዝግጅቶች ኅዳር 29 ቀን 2015 ዓ.ም እንደሚከበር መናገራቸውን ከአማራ ኮሙኒኬሽን ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።



## የስጋና ወተት ፍላጎትን ማሟላት የሚያስችል የምርምር ውጤት ለኅብረተሰቡ ተደራሽ እየተደረገ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የእንስሳትን ዝርያ በማሻሻል የዜጎችን የስጋና ወተት ፍላጎት ማሟላት የሚያስችል የምርምር ውጤት ለኅብረተሰቡ ተደራሽ እየተደረገ መሆኑን የደብረ ዘይት ግብርና ምርምር ማዕከል አስታወቀ።

የግብርና ሚኒስቴር መረጃ እንዳመለከተው፤ ኢትዮጵያ በእንስሳት ቁጥር ከአፍሪካ ቀዳሚ የሆነችና ለግብርና ምቹ የሆነ ስነ ምህዳር ያላት አገር ብትሆንም ዜጎች ከእንስሳት ሀብት በሚፈለገው ደረጃ ተጠቃሚ አልሆኑም።

መረጃው እንዳመለከተው፤ እንደ አገር 15 ሚሊዮን ላሞች፣ ስድስት ሚሊዮን ግመሎች፣ ወደ ሦስት ሚሊዮን የሚጠጉ ፍየሎች አሉ። ነገር ግን በአገር አቀፍ ደረጃ ያለው የስጋና ወተት ምርት ከፍላጎት ጋር ሲነጻጸር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም።

የደብረዘይት ግብርና ምርምር ማዕከል የእንስሳት ባዮ ቴክኖሎጂ ተመራማሪና ኃላፊ አቶ ሰይድ አሊ ለኢዜአ እንደተናገሩት፤ አንድ ላም በቀን የምትሰጠው የወተት ምርት በአማካኝ ከአንድ ነጥብ አምስት ሊትር አይበልጥም።

በኢትዮጵያ ካሉ የሚታለቡ ላሞች የሚገኘው ዓመታዊ ምርት 4 ነጥብ 9 ቢሊዮን ሊትር ሲሆን፤ ይህም ምርት ከዜጎች ፍላጎት 20 በመቶ የሚሆነውን ብቻ እንደሚሸፍን ተመራማሪው ገልጸዋል።

መንግሥት በቀጣይ አራት ዓመታት በሚተገበረው የሌማት ትሩፋት መርሐ ግብር ዓመታዊ የወተት ምርትን ወደ 11 ነጥብ 7 ቢሊዮን ሊትር ለማሳደግ እቅድ ማስቀመጡን አስታውሰው፤ ከዚህ አኳያ ማዕከሉ መርሐግብሩን በእንስሳት ባዮ ቴክኖሎጂ ምርምር ለማገዝ እየሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

በእንስሳት ባዮ ቴክኖሎጂ ምርምር በሰው ሰራሽ ማዳቀል፣ ጽንስ በማዘዋወርና በላቦራቶሪ ውስጥ ጽንስ በመፍጠር ቴክኖሎጂ የተሻሻሉ የወተት ላም ዝርያዎችን እያወጡ መሆኑን ጠቁመዋል።

በዚህም ከምርምር የወጡ የተሻሻሉ የወተት ላሞች ከአርሶ አደሩ ዘንድ በቀን እስከ 20 ሊትር እየሰጡ መሆኑን ገልጸው፤ በተሻሻለ ዝርያ ብቻ የሚፈለገውን ምርት ማግኘት ስለማይቻል በእንስሳት መኖ አመጋገብና ጤና ላይ ጭምር ምርምር እያደረግን ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያ ሰው ሰራሽ የእንስሳት ማዳቀል ሥራ የተጀመረው በ1938 ዓ.ም ቢሆንም የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎች ከሁለት በመቶ እንደማይበልጡ ተናግረዋል። የጽንስ ማዘዋወር ቴክኖሎጂም በሚፈለገው ደረጃ አጥጋቢ ውጤት ሲሰጥ አለመቆየቱን አስታውሰዋል።

በመሆኑም ማዕከሉ ዓለም ላይ ያሉ አገራት የሚጠቀሙበትን ቴክኖሎጂ በመያዝ ባለፉት ሁለት ዓመታት ብቻ ከ350 በላይ የወተት ጊደሮችን አላምደናል ብለዋል ባለሙያው።

የቦረና ላሞችን ከሆሊስቴይን ፍሬዥያን ጋር በማዳቀልና ዝርያቸውን በማሻሻል ምርትና ምርታማነታቸውን ማሳደግ ተችሏል ብለዋል።

የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ዳኘ ሞጆ፤ የእንስሳት ዝርያዎችን ለማሻሻያ ማስወለጃ የኮርማ አባላዘር ቴክኖሎጂ በመጠቀም ተጨባጭ ለውጥ አሳይተናል ማለታቸውን ኢዜአ ዘግቧል።



## ኬንያ በቀጣናዊ የሳይበር ደህንነት ዙሪያ ከኢትዮጵያ ጋር በጋራ ለመሥራት ፍላጎት እንዳላት ተገለጸ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የኬንያ የብሔራዊ ደህንነት አገልግሎት ከኢትዮጵያ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ጋር በሰው ኃይል ልማትና በቀጣናዊ የሳይበር ደህንነት ዘርፍ በጋራ ለመሥራት ፍላጎት እንዳለው ተገለጸ።

በኬንያ ብሔራዊ የደህንነት አገልግሎት የውጭ ደህንነት ዳይሬክተር ዶክተር ሰይፍ ሳሊም ሱለይማን የተመራ ልዑክ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር (ኢመደአ) ትናንት የሥራ ምልከታ አድርጓል።

ልዑኩ በጉብኝቱ በሳይበር ደህንነትና ሳይበር ቴክኖሎጂ ልማት ዙሪያ በኢመደአ እየተሠሩ ያሉ የቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት ሥራዎችን እንዲሁም የኢትዮ ሳይበር ታለንት ልማት ማዕከልን ተመልክቷል።

በሳይበር ደህንነት ዘርፍ ያለውን የሰው ኃይል እጥረት ለመቅረፍ ኢመደአ ከታዳጊዎች ጀምሮ እየሠራ ያለው ሥራ አበረታች መሆኑንም ልዑኩ ገልጿል።

የኬንያ የብሔራዊ ደህንነት አገልግሎት በሰው ኃይል ልማት እንዲሁም በቀጣናዊ የሳይበር ደህንነት ዘርፍ በጋራ ለመሥራት ፍላጎት እንዳለው ማስታወቁን ከኢመደአ የተገኘው መረጃ ያሳያል።

ልዑኩ በኢትዮጵያ ቆይታው የሳይበር ደህንነትን ቀጣናዊ ሰላምና ደኅንነት ለማረጋገጥ በሚደረጉ የጋራ ስምሪቶች ዙሪያ የተለያዩ ምክክሮችን እንደሚያደርግም ይጠበቃል።

# ክልሉ ሁሉም የመንግሥት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ አሳሰበ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሁሉም የመንግሥት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ አቅጣጫ አስቀምጦ እየሠራ መሆኑን የክልሉ ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ አስታወቀ። ቀልጣፋ፣ ጥራት ያለው እና ፍትሐዊ አገልግሎት ማግኘት የዜጎች መብት መሆኑንም ጠቁሟል።

ቢሮው ትናንት ባወጣው መግለጫ፣ በሕዝብ ይሁንታ ሥልጣን የያዘው መንግሥት በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እድገት የኅብረተሰቡን ብልጽግና ለማረጋገጥ ቀልጣፋ፣ ጥራት ያለው እና ፍትሐዊ አገልግሎት ለዜጎች መስጠት ግዴታው እንጂ እንደ ስጦታ የሚቆጠር ነገር አለመሆኑን አመልክቷል።

ኅብረተሰቡ አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችሉ መስፈርቶችን በማሟላት በየደረጃው ባሉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አስፈላጊውን አገልግሎት የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነው ያለው መግለጫው፤ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችም መስፈርቱን አሟልቶ ለሚመጣው ተገልጋይ በሕግ፣ በደንብ እና በመመሪያ መሠረት ግልጽና ፍትሐዊ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት ብሏል።

ከባለፉት አራት ዓመታት ወዲህ እንደ አገር የተጀመረውን የለውጥ ጉዞ ዳር ለማድረስ እና ሁለንተናዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ ሰፋፊ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። በተለይ የፖለቲካ ምሕዳሩን ማስፋት፣ አገሪቱ ያላትን መልካም ዕድሎችን በመለየት ጠንካራ ኢኮኖሚን መገንባት፣ ግብርናን ማዘመን፣ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እና ሕዝቦችን የሚያቀራርቡ በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን በመግለጫው ተብራርቷል።

ይሁን እንጂ ጥራት ያለው ቀልጣፋ አገልግሎትና ፍትሐዊ እስካልሆነና ከሌብነት እስካልጸዳ ድረስ በሁሉም መስክ የተሠሩ ሥራዎች ውጤታማ የመሆን ዕድላቸው አጠራጣሪ መሆኑን የጠቀሰው መግለጫው፤ አገሪቱ ለጀመረችው የለውጥ ጉዞ ትልቅ እንቅፋት ከሆኑት ችግሮች ውስጥ በአገልግሎት አሰጣጥ የሚስተዋለው ችግር አንዱ መሆኑን ገልጿል። ከዚህ አንጻርም በኦሮሚያ ክልል በአገልግሎት አሰጣጥ ትልቅ ችግር መኖሩን መንግሥት በጥናት መለየቱን መግለጫው አመላክቷል።

በጥናቱ መሠረት በክልሉ በየደረጃው ባሉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ግልጽነትና ፍትሐዊነት የጎደለው፣ ባለጉዳዮችን የማመላለስ አልፎ ተርፎም በሌብነት የተሞላ እንዲሁም በቴክኖሎጂ ያልታገዘ አገልግሎት አሰጣጥ መኖሩን ጠቅሷል።

እንደ መግለጫው፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር በሁሉም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚስተዋል ችግር ቢሆንም በተለይ ባለጉዳዮች የሚበዙባቸው መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ችግሩ የከፋ ነው። ከሁሉም በላይ ጉዳይ አስፈጻሚዎች/ደላላዎች በመሥሪያ ቤቶቹ ውስጥ እጃቸውን በመዘርጋታቸው ምክንያት ኅብረተሰቡ አገልግሎት የማግኘት መብቱ አደጋ ላይ ወድቋል ብሏል።

ችግሩ በመንግሥት በሕዝብ ግንኙነት ላይ ተጽእኖ ከማሳደሩ በተጨማሪ የለውጥ ጉዞውን የሚያደናቅፍና ሕዝቡን የሚያማርር መሆኑን በመገንዘብ መንግሥት ሁሉም መሥሪያ ቤቶች አገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ አቅጣጫን አስቀምጧል ብሏል።

ችግሩን ለመቅረፍ የተሰጠውን ኃላፊነት በመዘንጋት ባለጉዳዩን የሚያመላልስ፣ አገልግሎት በግሉ ጥቅም የሚመነዘር፣ ፍትሐዊነትን በመንፈግ ኅብረተሰቡን የሚያስለቅስ አመራርና ባለሙያ ለመግራት የተጠያቂነት ሥርዓት መዘርጋት ወሳኝ ጉዳይ ነው። ለዚህም መንግሥት በቁርጠኝነት ይሠራል ተብሏል።

የተጠያቂነት ሥርዓቱ እውን እንዲሆን ተገልጋዮችም ሆነ መላው ኅብረተሰብ ከመንግሥት ጎን እንዲቆም ጥሪ ቀርቧል። ኅብረተሰቡን አስፈላጊውን መስፈርት በማሟላት ለአገልግሎት ወደ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሲሄድ መብቱን ከማስጠበቅ በተጓዳኝ ፍትሕን የሚያጣምሙ አካላትን በማጋለጥ ተባባሪ እንዲሆንም በመግለጫው ተጠይቋል።

የአገሪቱ ሚዲያዎችም በአገሪቱ ቀልጣፋና ፍትሐዊ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲሰፍን የኅብረተሰቡ ዓይንና ጆሮ በመሆን በጉዳዩ ዙሪያ በትኩረት በመስራት ሙያዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ አሳስቧል።



ፎቶ - ሳሙኤል ተስፋዬ

# ኢፕድ የጀመራቸውና አገራዊ የለውጥ ሥራዎችን ለማስቀጠል የሚያግዙ ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ መሥራት ይገባል

## • ነባር የኢፕድ የሥራ አመራር ቦርድ ለአዲሱ ቦርድ የሥራ ርክክብ አካሄደ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጀመራቸው እና አገራዊ የለውጥ ሥራዎችን ለማስቀጠል የሚያግዙ ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ መሥራት እንደሚገባ ተጠቆመ። የኢፕድ ነባር የሥራ አመራር ቦርድ ለአዲሱ ቦርድ አባላት የሥራ ርክክብ አካሂዷል።

የቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ አቶ አወሉ አብዲ ነባሩ የሥራ አመራር ቦርድ አዲስ ለተሰየመው የሥራ አመራር ቦርድ በትናንትናው ዕለት የሥራ ርክክብ ባካሄደበት ወቅት እንደገለጹት፤ ነባሩ ቦርድ በተቋሙ በነበረው የለውጥ ተግባራት ሥራዎች ላይ ውሳኔዎችን እያሳለፈ ድርጅቱ አሁን ለደረሰበት ደረጃ አድርሷል።

አዲሱ የሥራ አመራር ቦርድም በነባሩ የሥራ አመራር ቦርድ በጅምር ተይዘው የነበሩ ሥራዎችን ዳር ሊያደርስ ይገባል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ቀደም ሲል ከነበረበት አስቸጋሪ ሁኔታ ተላቆ በለውጥ ሂደት ላይ ይገኛል ያሉት አቶ አወሉ፤ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ተወዳዳሪ ሚዲያ ሆኖ መምጣቱንም ለአዲሱ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ባደረጉት ገለጻ አመላክተዋል። ድርጅቱ አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎችን ይዞ እየሠራ መሆኑንም አንስተዋል። «ኢትዮጵያ እያሸነፈች ትሻገራለች» በሚል መሪ ቃል የሚያደርገው ስለኢትዮጵያ የፎቶግራፍ አውደርዕይና የፓናል ውይይት ለዚህ እንደማሳያ መሆኑንም አንስተዋል። ድርጅቱ በይዘት ሥራዎቹም ተዓማኒና ተጠቃሽ የሚዲያ ተቋም ሆኖ መምጣቱንም ባደረጉት ገለጻ አንስተዋል።

ለድርጅቱ አዲስ የተሰየመው ቦርድም ነባሩ የሥራ አመራር ቦርድ በጅምር ይዟቸው የነበሩ ተግባራትን ዳር ማድረስ ይገባዋል ብለዋል።

ድርጅቱ የራሱ ማተሚያ ቤት እንዲያቋቁም፣ የቴሌቪዥን አማራጭ እንዲኖረው መሥራት፣ የሠራተኞችና አመራሩን ግንኙነት እንዲጠናከር መሥራት ለአብነት የጠቀሷቸው ናቸው።

የነባሩ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ባደረጉት ንግግርም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በአሁኑ ወቅት በጥሩ መሠረት ላይ መሆኑን አንስተዋል። ተቋሙ ያለውን ሀብት እና የያዘውን ታሪክ በተገቢው ሁኔታ ጥቅም ላይ ለማዋል በቀጣይ መሥራት እንደሚገባውም ጠቅሰዋል። ድርጅቱ የራሱ ማተሚያ ቤት አለመኖሩ በሕትመት ዋጋ መናር የሚደርስበት ጫና ከፍተኛ መሆኑን የጠቀሱት የነባሩ የቦርድ አባላት፤ በቀጣይ ድርጅቱ የራሱ ማተሚያ ቤት እንዲኖረው መሥራት እንደሚገባውም አንስተዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጌትነት ታደሰ በበኩላቸው፤ ነባሩ የሥራ አመራር ቦርድ በድርጅቱ የአሠራር ማሻሻያ እንዲኖርና የሥራ መመሪያዎች እንዲጸድቁ ላሳለፈው ውሳኔ እንዲሁም ለድርጅቱ ሠራተኞች ሲያደርግ ለነበረው የማነቃቃያ ሥራ አመስግነዋል።

ባለፉት ሦስት ዓመታት ድርጅቱ እቅዶችን ለጥጦ በመሥራቱ ውጤት እንዲያስመዘግብ አስችሎታል ያሉት አቶ ጌትነት፤ አዲሱ የሥራ አመራር ቦርድም ድርጅቱ ይህን አጠናክሮ እንዲቀጥል አቅም እንደሚሆንለት ገልጸዋል።

የአዲሱ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ምህረት ደበበ (ዶ/ር) የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሠራተኞች ያዘጋጁትን ስጦታ ለቀድሞ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት አበርክተዋል።



አቶ ሳሊ ሙሐመድ



ወጣት ዘሳለም ዮሐንስ



ወይዘሮ ሰብለ መላኩ

# ሙዚየሙ ዲጂታል ኢትዮጵያን በዓይነ ህሊናችን እንድናይ አድርጎናል

- ጎብኚዎች

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- በሳይንስ ሙዚየሙ የቀረቡ የፈጠራ ውጤቶችና ቴክኖሎጂዎች ለኢትዮጵያ እድገት በር ከፋችና ዲጂታል ኢትዮጵያን በዓይነ ህሊናችን እንድናይ የሚያደርግ ነው ሲሉ የሳይንስ ሙዚየምን የጎበኙ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ተናገሩ።

ሙዚየሙን ሲጎበኙ የነበሩ ወይዘሮ ያስሚን የሱፍ እንደተናገሩት፤ በሙዚየሙ የቀረቡ የፈጠራ ውጤቶችና ቴክኖሎጂዎች የወደፊቷን ዲጂታል ኢትዮጵያ በዓይነ ህሊናችን እንድናያት አድርጓል። ኢትዮጵያ በሳይንስና ቴክኖሎጂው ታግዛ በውትድርና፣ በአቅርቦት ሰንሰለት፣ በፋይናንስና በሳይበር ደህንነት እያደገች ከመጣች በሳይንስና ቴክኖሎጂው ዘርፍ ውጤታማ ከሆኑ አገራት የምትደርስበት ጊዜ ቅርብ ነው።

የዲጂታል ኢትዮጵያ መምጣት ትምህርት በቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ስለሚያደርግ በዘርፉ የተሻለ ሥራ እንዲሠራ የሚያደርግና ልጆች የተሻለ እውቀት የሚያገኙበትን ሁኔታ የሚያመቻች ነው።

ሙዚየሙን ሲጎበኝ ያገኘነው አቶ ሳሊ ሙሐመድ በበኩሉ፣ «አንዳንድ ጎብኚዎች በሳይንስ ሙዚየሙ የቀረቡት የቴክኖሎጂ ውጤቶች የቅንጦት ናቸው ይላሉ፤ ነገር ግን ሙዚየሙ ለኢትዮጵያ እድገት ወሳኝና አንገብጋቢ እንዲሁም በር ከፋች ነው» ብሏል።

80 በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ገበሬ ሆኖ ሳለ እስከ አሁን ድረስ እራስን መመገብ አልተቻለም ያለው አቶ ሳሊ፣ አሁን ግን ግብርናው በሳይንስና ቴክኖሎጂ የሚደገፍ ከሆነ 3 እስከ 5 በመቶ የሚሆነው ነዋሪ ገበሬ የአገሪቱን ነዋሪ በሙሉ መመገብ ይችላል ብሏል።

በህክምና፣ በውትድርና እና በማዕድን ዘርፍ የቀረቡት የቴክኖሎጂ ውጤቶች የኢትዮጵያ እድገት ከምን ጊዜውም በላይ ቅርብ እንዲሆን ያስቻሉ መሆኑንም ጠቁሟል።

ከህምናው ዘርፍ ጋር በተያያዘ ቤተ ሙከራ ሳትገባ የተለያዩ ኬሚካሎችን ምን ጉዳት እንደሚያደርሱና ምን ዓይነት ጥቅም እንዳላቸው ቴክኖሎጂን በመጠቀም ማወቅ ይቻላል። ይህም የሚደረገው ሰው ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት ሳይደርስ ነው። ይህም ቴክኖሎጂ በሳይንስ ሙዚየሙ ቀርቧል ሲልም አክሏል።

እንደ አቶ ሳሊ ገለፃ፣ ከዚህ በፊት የነበረውን የትምህርት ሥርዓት በአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች የሚለውጥና የሚቀይር ከሆነ ተማሪዎች ለትምህርቱ ትኩረት ሰጥተው እንዲማሩና ትምህርቱ እንዲገባቸው ያደርጋል። ይህም የተማሪዎች የፈጠራ ሥራቸው እንዲያድግ የበኩሉን አስተዋጽዖ ያደርጋል። ስለዚህ የሚመጣው ትውልድ የተሻለ እውቀት የሚኖረው ከሆነ የወደፊቷን ኢትዮጵያን መሥራት ይቻላል።

ተማሪዎች ማወቅ ያለባቸውን በድምጽና በምስል ታግዘው እንዲማሩ የሚያስችል ቴክኖሎጂ በሙዚየሙ ቀርቧል ያለው አቶ ሳሊ፣ የሳይንስ ሙዚየሙ የተሠራበት አላማ ኅብረተሰቡን ከቴክኖሎጂ ጋር ለማቀራረብ ነው። ነገር ግን ሙዚየሙን የሚጎበኙ ሰዎች ሙዚየሙን እየተጠቀሙበት ያለው ፎቶ ለመነሳት ነው ብሏል።

በሙዚየሙ የቀረቡት ቴክኖሎጂዎች በተለያዩ አገራት ሲጠቀሙባቸው የነበሩ ቴክኖሎጂዎች ቢሆኑም ወደ ኢትዮጵያ መግባታቸው ኢትዮጵያን ከሌሎች አገራት ጋር ተፎካካሪ ያደርጋታል ያለው ደግሞ ወጣት ዘላለም ዮሐንስ ነው።

ኢትዮጵያ በሳይንስና ቴክኖሎጂው ዘርፍ ከሌሎች አገራት እኩል መሆን አለባት። ምክንያቱም ዘመኑ የቴክኖሎጂ በመሆኑ በሳይበርና መሰል የቴክኖሎጂ ውጤቶች አገራችን እንዳትጠቃና በሌሎች ተጽዕኖ ስር እንዳትውድቅ ሁሉም ወጣት የበኩሉን ሊወጣ ይገባል ብሏል።

ወይዘሮ ሰብለ መላኩ በኩላቸው፣ ልጆች በቴሌቪዥን የሚያዩትን በአካል እንዲያዩት ማድረግ የተሻለ ቴክኖሎጂ ለመሥራት ያግዛቸዋል ብለዋል።

ሙዚየሙ የቀረቡት ቴክኖሎጂዎች ኢትዮጵያ ከበፊቱ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገችና እየበለጸገች እንደመጣች ማወቅ ችያለሁ። እናም በጣም ደስ ብሎኛል። እየተሠራ ያለው ሥራ እጅግ የሚበረታታና ቀጣይነት ያለው እንደሚሆን አልጠራጠርም ብለዋል።

ዜና

# ስሰላም ስምምነቱ ተግባራዊነት ሁሉም አካላት አወንታዊ ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ለፕሪቶሪያውን የሰላም ስምምነት ተግባራዊነትና ስኬት ሁሉም አካላት የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት እንደሚጠበቅባቸው ተገለጸ። የፕሪቶሪያውን የሰላም ስምምነትን በተመለከተ የፌዴራል ተቋማት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ውይይት አካሂደዋል።

የፌዴራል ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች ትናንት በብልጽግና ፓርቲ ጽሕፈት ቤት የመሰብሰቢያ አዳራሽ ለሰላም ስምምነቱ በመንግሥት በኩል ስለተደረገው አጠቃላይ ዝግጅት፣ የሰላም ስምምነቱ ጭብጦች፣ የስምምነቱ አጠቃላይ እንድምታ እና በቀጣይ ትኩረት በሚሹ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት አካሂደዋል።

በውይይቱ በመንግሥት በኩል ለሰላም የነበረው የወትሮ ዝግጁነትና ቁርጠኝነት ብሎም ለፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ስኬታማነት አስቀድሞ የተደረገው ዝግጅት እጅግ አመርቂ እንደነበር ተመላክቷል።

በሰላም ስምምነቱ ደስተኛ ያልሆኑ የተለያዩ ድምጾች በየአቅጣጫው እየተስተዋሉ እንደመሆኑ መጠን ሁሉም አካላት ለሰላም ስምምነቱ ተግባራዊነት እና ስኬት የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት እንዳለባቸው ተነስቷል።

ጥላቻ፣ በቀልና የክፋት መንገድ እንደ አገር እንደማያዋጣን ታሪካችን ምስክር ነው ያሉት ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፤ ባለፉት ጊዜያት የተፈጸሙ ቁርሾዎችና ህመሞችን ማከም፣ መጪውን ጊዜ ታሳቢ ያደረገ የልማት፣ የዕድገት እና የብልጽግና ጉዞ መከተል ተገቢ መሆኑን አንስተዋል።

የሠላም ስምምነቱ እንዳይደናቀፍ ማድረግ ከዚሁ አገራዊ ራዕይ አኳያ መታየት እንዳለበት የመድረኩ ተሳታፊዎች አጽንኦት ሰጥተው መክረውበታል።

ስምምነቱ በአገር ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ላይ የተደቀነውን አደጋ መቀልበስ የሚያስችል፣ ጦርነቱን በዘላቂነት በማቆም ዘላቂ ሰላም መገንባት በሚያስችል ሁኔታ የተፈፀመ መሆኑም የሥራ ኃላፊዎች ጠቁመዋል።

ስምምነቱ ለአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በተለይ በጦርነቱ ቀጥታ ተጠቂ ለነበሩ የትግራይ፣ አማራና አፋር ሕዝብ ዕረፍት የሚሰጥ እንደሆነና የኢትዮጵያን አሸናፊነት ያረጋገጠ እንደሆነም የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎቹ በውይይታቸው አንስተዋል።



ፎቶ - ሳሙኤል ተስፋዬ

ኢትዮጵያ በግንባር ቀደምትነት የምታቀነቅነውን «ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄ» የሚለውን አቋም ወይም የፓን አፍሪካኒዝም እሳቤዎችን በሚያፀና መንገድ የተፈጸመ እንደሆነም ጠቁመዋል።

ስምምነቱ ለኢትዮጵያ አዲስ የፖለቲካ ባህልና የታሪክ ምዕራፍ መጀመር ያበሰረ በመሆኑ እንዲሁም እንደ አገር ወደ ሕገመንግሥታዊነትና ሕጋዊነት የሚመልስ አቅጣጫ በመያዙ እንድምታው የላቀ መሆኑም በውይይቱ ተመላክቷል።

በጦርነት፣ በዲፕሎማሲና በሰላም ስምምነቱ ሂደት የተገኙ ስኬቶችን በማስቀጠል በፖለቲካው እና በልማት ዙሪያ ተመሳሳይ ድል ለማስመዝገብ ሁሉም የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በአንድነት ሊረባረቡ እንደሚገባ በመድረኩ ተገልጿል።

በከፍተኛ መስዕዋትነት የተገኘው አገራዊ ድል በሁሉም ዘርፎች ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበትም አቅጣጫ ተቀምጧል።

ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎቹ በውይይታቸው የሰላም ስምምነቱ ስኬታማ እንዲሆን በከፍተኛ መስዋዕትነት ዋጋ ለከፈሉ የአገር መከላከያ ሰራዊት፣ በከፍተኛ ብቃት አመራር ለሰጡት ለኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንዲሁም በሰላም ንግግሩ ሂደት ተሳታፊ ለነበሩ አካላት ምስጋና አቅርበዋል።

# ተሰርዞ የነበረው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ውስጥ ተካተዋል ተብሏል።

በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ቢሮ ኃላፊ ያስሚን ወሃቢረቢ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ የከተማ አስተዳደሩ የ20/80 14ኛ ዙር እና የ40/60 3ኛ ዙር የጋራ መኖሪያ ቤት ዕጣ አወጣጥ ሥነሥርዓት በዛሬው ዕለት ከስምንት ሰዓት ጀምሮ ይከናወናል።

ቀደም ሲል ሐምሌ 1/2014 ዓ.ም. የ20/80 14ኛ ዙርና የ40/60 3ኛ ዙር የዕጣ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት በይፋ መካሔዱን አስታውሰው፤ ባጋጠመ የወንጀል ጥቆማ መሠረት በተደረገ ኦዲት ዕጣው ሙሉ ለሙሉ እንዲሰረዝ ተደርጎ በጉዳዩ የተጠረጠሩ አካላትም በሕግ አግባብ እንዲጠየቁ መደረጉን አንስተዋል።

ቢሮ ኃላፊዋ በመግለጫቸው፤ በጉጉት ሲጠባበቅ የነበረውን ኅብረተሰብ እጅግ ያሳዘነ ቢሆንም የተሠራው ሕገወጥ ተግባር ተቀባይነት የሌለውና የብዙኃኑን ጥቅም በእጅጉ የሚጎዳ ስለነበር ዕጣው መሠረዙ አማራጭ አልነበረውም። ከተማ አስተዳደሩ ጉዳዩን ከተለያዩ ተቋማት ለተውጣጡ ባለሙያዎች ክፍት አድርጎ ኦዲት ያደረገበት አሠራር የከተማ አስተዳደሩን ቁርጠኝነት ያሳየ እንደነበርም ገልጸዋል።

የከተማ አስተዳደሩ በይፋ ለሕዝቡ ቃል በገባው መሠረት ቤቶቹን ባጠረ ጊዜ የተፈጠሩ ችግሮቹን በሚያርም አግባብና ደህንነቱን በጠበቀ መልኩ የዕጣ ማውጫ ሥርዓቱን በማልማት የመረጃ ማጥራትና ማደራጀት ሥራና ሌሎች የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በማከናወን ለዕጣ ዝግጁ ማድረጉን ተናግረዋል።

በ20/80፤ 18ሺ 930 ቤቶች፤ በ40/60፤ 6 ሺ 843 ቤቶች በድምሩ 25,791 ቤቶች ዕጣ የሚወጣባቸው ሲሆን፣ ቀደም ብሎ ከፍተኛ ጥያቄ ሲቀርብበት የነበረውን የባለ 3 ሦስት መኝታ ቤት ተመዝጋቢዎችን ጉዳይ ምላሽ ለመስጠት ተጨማሪ 300 ቤቶችን ቀሪ ሥራ በማከናወን ለነባርና አዲስ ተመዝጋቢዎች በዕጣ ለማስተላለፍ ዝግጁ ኃላፊዋ ጠቁመዋል።

እንደቢሮ ኃላፊዋ መግለጫ፤ ዕጣ ማውጫ «ሲስተሙ» በአዲስ መልክ ከፍተኛ ልምድ ባለው በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር እንዲለማ ተደርጓል። «ሲስተሙ» አርተፊሻል ኢንተለጀንስ፣ አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፣ ከከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የተካተቱበት ቴክኒካል ኮሚቴ በድጋሚ በመፈተሽ የማረጋገጥ ሥራ መሠራቱን አስረድተዋል።

የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ዳይሬክተር አቶ ሽመልስ ታምራት በበኩላቸው፤ በዕጣው ብቁ የሚሆኑትም የ20/80 ባለ አንድና ባለ ሁለት ነባር የ1997 ዓ.ም ተመዝጋቢዎች በመመሪያው መሠረት ዝቅተኛውን የ60 ወራት ቁጠባ መጠን እንዲሁም የባለ 3 መኝታ ነባርና አዲስ ተመዝጋቢዎች 2005 ዓ.ም ዝቅተኛውን የ84 ወራት ቁጠባ መጠን ያሟሉ ናቸው።

በተጨማሪም የ40/60 ተመዝጋቢዎች ከ40 በመቶና ከዚያ በላይ ቁጠባ ያላቸው ለዕጣ ውድድር ብቁ የሆኑ እስከ የካቲት 21/2014 ዓ.ም ድረስ መስከረም 9 ቀን 2015 ዓ.ም ከባንክ በተገኘው መረጃ ላይ ተመስርቶ የመረጃ ማጥራት ሥራ በተቋቋሙ 9 አባላት ባሉት ኮሚቴ 146 ሺ 892 ተመዝጋቢዎች ለዕጣ ብቁ ሆነው መገኘታቸውን ገልጸዋል።

ዛሬ የሚወጣው የዕጣ ማውጣት ሥነሥርዓት 400 የሚሆኑ የተለያዩ ታዛቢዎች በተገኙበት የሚካሄድ ሲሆን፣ ችግሮች እንዳይፈጠሩ የቤት መረጃ፣ የቆጣቢዎች መረጃና ሌሎች አሠራሮችን ያካተተ አራት ሞጁሎች ባሉት ደህንነቱ የተጠበቀ አሠራር ተከትሎ ይወጣል ብለዋል።

# ኢትዮጵያ ስመጀመሪያ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኢትዮጵያን ማዕከል ያደረገ የደን ሽፋንና በጊዜው ውስጥ የሚኖረውን ለውጥ ለመከታተል የሚያስችል መተግበሪያም እንዲሁ ሳተላይቷ በሰጠችው መረጃ አማካኝነት ማልማት እንደተቻለ ገልጸዋል።

በየጊዜው ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ጋር የተገናኙ መረጃዎችንም በግብዓትነት ለመጠቀም እንደተቻለ፤ በቱሪዝም ዘርፍ በተለይም በደቡብ ኦሞና በጋሞ ዞን የቱሪዝም ካርታ ለማዘጋጀትና ከዚህ ሥራ ጋር የሚገናኙ መተግበሪያዎችን የማበልጸግ ሥራዎችም በግብዓትነት ጥቅም ላይ መዋላቸውን ተናግረዋል።

ከዚህም ባሻገር በኢትዮጵያ ውስጥ ለጥጥ እርሻ አመቺና ተስማሚ የሆኑ ቦታዎችን ለመለየት የETRSS-1 ሳተላይት መረጃ በግብዓትነት ማገልገሉን ዳይሬክተሩ ጠቅሰዋል። በሳተላይቷ አማካኝነት ለተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችና የምርምር ተቋማት ለምርምር ሥራ የሚሆኑ መረጃዎችን የመስጠት ሥራ እንደተከናወንም ጠቁመዋል።

አቶ አብዲሳ፤ መረጃውን ከመጠቀም አንጻር የተፈጠረው አቅም የተሳካ እንደነበርም ነው ያስታወቁት። ከዚህ ባሻገር የተፈጠረ የቴክኒክ አቅም መኖሩንም ተናግረዋል።

ወጣት መሐንዲሶች ከንድፍ ሥራ ጀምሮ ተሳትፎ ማድረጋቸውንና ሳተላይቷ ከመጠቀች በኋላ ከምድር ሆኖ የመቆጣጠርን ሥራ በወጣት ባለሙያዎች ቁጥጥር ሲደረግ መቆየቱን፤ ይህም የኦፕሬሽን አቅም መፍጠሩን ነው የጠቀሱት። የጥገናና አገልግሎት ሥራዎችን በተሳካ መልኩ ለማከናወን እንደተቻለም አንስተዋል።

አቶ አብዲሳ፤ «በቀጣይ አልምተን እናመጥቃለን ብለን የምናስበው ETRSS-2 የከፍተኛ ሪዞሉሽን የመሬት ምልከታ ሳተላይት ነው» በማለት፤ «ቀጥሎ ለሚሠራው ሥራ መነሻ የሚሆን ነገር ተገኝቷል። በልምምዱ ቀጥሎ ለምናለማው ሳተላይት ምን መምሰል አለበት የሚለውን ለመለየት አስችሎናል። የመጀመሪያም ብንሆን ስለ ሳተላይት ዝርዝር ባህሪ፣ ስለ ቴክኖሎጂው ዓይነትና ምንነት ለመረዳት አስችሎናል» ሲሉ ገልጸዋል።

# «በጦርነቱ የቆሰሉ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደ አቶ ኤርሚስ ገለጻ፤ ጦርነቱ ሰዎች ራሳቸውን እና ማህበረሰቡን የሚመለከቱበትን ዕይታ ጎድቷል። የስነልቦና ተፅዕኖ አስከትሎ አልፏል፤ የአዕምሮ ቁስል አስከትሏል፤ ቤተሰቦቻቸውን ያጡ እና የተደፈሩ ሴቶች ቤተሰባቸውን ብቻ ሳይሆን ራሳቸውንም ጭምር ያጡ በመሆናቸው፤ መጀመሪያ ጦርነቱ የአዕምሮ ቁስል ፈጥሮ ማለፉን በማመን እና በመቀበል በዘመቻ ከዚህ ቁስል የሚድኑበት መንገድ ሊፈጠር ይገባል።

አቶ ኤርሚያስ እንደገለጹት፤ የዓለም ተሞክሮም ሆነ የጥናት ውጤቶች እንደሚሳዩት ብዙ ጊዜ ጦርነት ከተከሰተ በኋላ ሰዎች ድብርት ውስጥ ይገባሉ። እየባሰ ሲመጣ መቀወስ ደረጃ ላይ ይደርሳሉ። በመጨረሻም ራሳቸውን እስከማጥፋት ይደርሳሉ። ሕይወት ትርጉም አልባ ይሆንባቸዋል። ግለሰቦች አዕምሯቸው ይፈርሳል። የግለሰብ አዕምሮ ሲጎዳ እና ግለሰቦች የአዕምሮ ቁስል ሲያጋጥማቸው የማህበረሰብ መስተጋብር ይናጋል። የግለሰብ ብቻ ሳይሆን የማህበረሰብ ዋና ነገርም ይፈርሳል። ይሔ ደግሞ ሰውየው ላይ ብቻ አይቆምም፤ ወደ ትውልድ ይሻገራል።

ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገር የአዕምሮ ቁስለት (trans generational trauma) እንዳይከሰት ከወዲሁ ጠንክሮ በመሥራት የአዕምሮ ህክምናን ተደራሽ ማድረግ ያስፈልጋል ያሉት አቶ ኤርሚያስ፣ ያለበለዚያ እናት በጦርነት ያሳለፈችው መጥፎ አጋጣሚ፣ በጦርነቱ ምክንያት ያጋጠማት የአዕምሮ ቁስለት፣ በጦርነቱ ምክንያት የተፈጠሩባት የተዛቡ አስተሳሰቦችን ለልጇ ታወርሰዋለች። ስለዚህ ጦርነቱ አንድ ወቅት ብቻ ሆኖ የሚበቃ ሳይሆን ተፅዕኖው እስከ የልጅ ልጅ ድረስ ይዘልቃል። ይህ በዘላቂነት አገር ላይ ጉዳት ያስከትላል ብለዋል።

በመቀሌ፣ በኮምቦልቻ፣ በደሴ፣ በሃይቅ እና በጎንደር አካባቢ በጦርነት ምክንያት የተጎዱ፣ የተፈናቀሉ ወገኖች ባሉበት ቀርበው የበጎ ፈቃደኝነት ሥራን ሲያከናውኑ መክረማቸውን አስታውሰው፤ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ጦርነት በተካሔደባቸው ቦታዎች እንደሚያጋጥመው ሁሉ በኢትዮጵያም ጦርነት ማህበረሰብ ያለውን ጤናማ አስተሳሰቡን እና አመለካከቱን የሚያጣበት መጥፎ ሁኔታን የሚፈጥር ነው። ስለዚህ ጦርነት የማህበረሰብን ጤናማ ጉዞ እንዳይገታ እና ማህበረሰብን ወዳልተፈለገ የሕይወት አጋጣሚ እንዳይመራ አስቀድሞ መሥራት እንደሚገባ አብራርተዋል።

«ሰው ሰው የሚሆነው በአዕምሮው ነው። ሰው ዓይኑ ቢጠፋ ሕይወት ይቀጥላል፤ እጁ ቢቆረጥ እግሩ ቢቆረጥ ሕይወት ይቀጥላል፤ አዕምሮ ከተጎዳ፣ አዕምሮ ከቆሰለ፣ አዕምሮ ከታመመ፣ አዕምሮ ከተናጋ እና አዕምሮ የመጀመሪያ ሥራውን ለመሥራት ከተቸገረ የግለሰብ ሕይወት ብቻ ሳይሆን ማህበረሰብም እንደማህበረሰብ ለመቀጠል ይቸገራል» ብለዋል።

«አሁን ያለንበት ወቅት ኢትዮጵያን ለማሻገር በዋናነት የሚያስፈልገው የስነልቦና ጤንነት እንደሆነ ግልፅ ነው።» ያሉት የስነልቦና ባለሙያው በቂምና በበቀል ውስጥ የገቡ እና ተስፋቸውን ያጡ መኖራቸውን ከማህበረሰቡ ጋር ሲሠሩ ማየታቸውን ተናግረዋል። እናታቸው ወይም አባታቸው ከቤት ሊወጡ ሲሉ የሚከለክሉ ሕፃናትን ማየታቸውን፤ «ከቤት አትውጪብኝ ትሞችብኛለሽ» ብለው የሚያለቅሱ፤ የ11 ዓመት፣ የ12 ዓመት እና የ13 ዓመት ልጆች ሆነው አልጋ ላይ የሚሸኑ እና መረጋጋት ያልቻሉ ሕፃናትን መመልከታቸውን ተናግረዋል።

በመጨረሻም «እናቶች በጤና ተቋማት እንዲወልዱ በዘመቻ አስገራሚ ሥራ ተሠርቷል። ጤና ጣቢያዎቻችን እና ሆስፒታሎቻችን እናቶች በጤና ተቋማት እንዲወልዱ በሚል እንደተካሔደው ዘመቻ ለአዕምሮ ህክምና ቦታ ሊኖራቸው ይገባል። ተደራሽ መሆንም አለባቸው።» ያሉት የስነልቦና ባለሞያው፤ በዘመቻ መልኩ አዕምሮ ህክምና ላይም መሠራት አለበት። እነዚህ የተረበሹ ስነልቦናዎች ካልታከሙ ግን ከትናንትናው በላይ የነገው ያስፈራል ብለዋል።

## ርዕሰ አንቀፅ

# ለዘላቂ ሰላም በኅብረት እንትጋ!

ሰላም ዋጋው በቀላሉ የማይተመን ትልቅ እሴት ነው። በተለይም ነገን በብዙ ተስፋ ለሚጠብቅና ለዚህም የትኛውንም ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ ለሆነ ሕዝብ ዋጋው አልፋና ኦሜጋ እንደሆነ ይታመናል። ከዚህም የተነሳ ስለ ሰላም የሚከፈል ዋጋ ትርጉሙ ከፍ ያለ፤ ጥልቅ ጭምር ነው።

በተለይም እንደኛ ላለ የሰላም እጦት በየዘመኑ ብዙ ዋጋ ላስከፈለው፤ ከትናንት ብቻ ሳይሆን ከዛሬ ችግሮቹ በስተጀርባ ትልቅ አቅም ሆኖ ለሚፈታተነው ማህበረሰብ፤ የሰላምን ጉዳይ ማቅለልም ሆነ፤ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት አሳንሶ ማየት ተገቢ አይደለም።

በየትኛውም ምክንያት፤ ለየትኛውም ዓላማ የሚካሄድ ጦርነት አውዳሚ ነው። ሊያስከትል የሚችለው ሰብአዊ ሆነ ቁሳዊ ጥፋት ጦርነቱ የሚካሄድበትን ማኅበረሰብ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ በነባር ቀደምትነት መጉዳቱ የማይቀር ነው።

ዓለም አሁን ካለችበት ትስስር አንጻር እውነታው ከዚህም በላይ አካባቢያዊና ዓለም አቀፍ ይዘት ሊኖረው ይችላል። ይህም ዛሬ ዛሬ በግልጽ እየታየ ያለ ዓለም አቀፋዊ ክስተት ነው። ስለ ጦርነትና ጦሱ ለኛ ኢትዮጵያውያን አስተማሪና አስረጅ የሚያስፈልገን ሕዝቦች አይደለንም፤ ጦርነት በየዘመኑ ከፍ ያለ ዋጋ ካስከፈላቸው ሕዝቦች መካከል ተጠቃሽ ነን። የትናንት ብቻ ሳይሆን የዛሬውንም ህይወታችን እየተፈታተነ ያለው ማህበራዊ ችግርም ነው።

ከትናንት የግጭትና የርስ በእርስ ጦርነቶቻችን መማር አለመቻላችን፤ በየዘመኑ የነበሩ ትውልዶችን ዋጋ አስከፍሏል፤ ይህም ትውልድ በተመሳሳይ መልኩ ከትናንት መማር ባለመቻሉ ከቀደሙት ዘመናት በከፋ መንገድ ዋጋ ለመክፈል ተገድዷል።

ስለ ዴሞክራሲ እና የሀሳብ የበላይነት ገዝፎ በሚደመጥበት በዚህ ዘመን፤ ችግሮቻችንን በኃይል /በጠብመንጃ ለመፍታት የሄድንበት መንገድ የቱን ያህል ዋጋ እንዳስከፈለን ዛሬ ላይ ሆነን ለመገመት የሚከብደን አይደለም። መንገዱ ከአቅማችን በላይ ያሸከመን የቤት ስራም ገና አልተጀመረም። ቀጣይ ዓመታትን ሊጠይቀን እንደሚችልም ይታመናል።

ችግሩ በተለይም በለውጥ መነቃቃት፤ ብዙ ተስፋ ሰንቀን አገራዊ ጉዞ በጀመርን ማግስት የገባንበት መሆኑ ካስከፈለን ሰብአዊና ቁሳዊ ዋጋ ባልተናነሰ መልኩ፤ በለውጥ መንፈስ የሰነቅነውን ተስፋ በማቀጨጭ፤ እንደ አገር የፈጠረብን የልብ ስብራት በቀላሉ የሚታሰብ አይደለም።

በረጅም የታሪክ ምእራፋችን ውስጥ ይዘነው የመጣነው ችግሮችን በኃይል የመፍታት /የአሸናፊ ተሸናፊ ትርክትን የማስቀጠል የደመነፍስ አካሄድ፤ በዚህም ዘመን ከግጭት አዙሪት የመውጣት ዕድላችንን ከእጃችን ተናጥቆናል። ለመጪው ትውልድ አዲስ /ሰላማዊ የችግር አፈታት ባህል ማውረስ የሚያስችለንን አጋጣሚ አሳጥቶናል።

አባቶች "የፈሰሰ ውሃ አይታፈስ "እንደሚሉት ትውልዱ ዘመኑን ከገዛው ችግሮችን በሰላም የመፍታት የአስተሳሰብ ከፍታ ውስጥ ተገኝቶ ወደ ግጭት ባይገባ መልካም ነበር፤ ይህ ግን አልሆነም። ከዚህም የተነሳ ውድ ዋጋ ተከፍሏል።

አሁን ግን ከትናንት /ከቀደመው ትውልድና የአሁኑ ጦርነት ካደረሰው ጥፋት በመማር ራስን ከተጨማሪ ጥፋት ማቀብ ይገባል። ከየትኛውም ግላዊና ቡድናዊ አስተሳሰብ ወጥቶ አገርና ህዝብን ለሚጠቅም አጀንዳ እራሱን ተገዥ ማድረግ ይኖርበታል።

ከመጠፋፋት /ከአሸናፊ ተሸናፊ ትርክት ወጥቶ ትውልዱን /አገርን አሸናፊ ለሚያደርግ እውነታ ራሱን አሳልፎ መስጠት፤ በዚህም የአዲስ ታሪክ ባለቤት በመሆን፤ አገርና ህዝብን መካስ ይኖርበታል። ለዚህ ደግሞ ከሁሉም በላይ አገርን አሸናፊ ላደረገው የሰላም ስምምነት ተገዥ መሆን ይጠበቅበታል።

ለጀመርነው፤ ሕዝባችን ብዙ ዋጋ ከፍሎ ከፍ ባለ ተስፋ በጉጉት ለጠበቀውና ለሚጠብቀው ልማት፤ ከዚህ ለሚመነጭ ብልጽግና እና ተጨማሪ ብሄራዊ ክብር የቱን ያህል የማይተካ አቅም እንደሆነ በመረዳት መላው ህዝባችን ዘላቂ ሰላም የሚጠይቀንን መስዋእትነት ሁሉ ለመክፈል የሚያስችል ዝግጁነት መፍጠር ይኖርበታል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

# የተጀመረውን የሠላም መንገድ የበለጠ ፍሬያማ እንዲሆን

**ዶክተር ጀኔኑስ**

ዓለማችን ከተፈጠረችበት ጊዜ አንስቶ እጅግ በጣም አስከፊ ሁኔታዎችን አሳልፋለች። አንዳንዶች በታሪክ ምዕራፍ ተከፋፍለው ተፅፈዋል፤ ሌሎች ደግሞ ትኩረት ሳይሰጣቸው አሊያም ሆን ተብለው ታልፈዋል። እነዚህ የታሪክ ምዕራፎች ሲከፈቱ ብዙ ነገሮች ይታያሉ፤ ይሰማሉ።

በነዚህ ታሪኮች አለማችን እጅግ ዘግናኝ የሚባሉ ግፎችን አስተናግዳለች። አንዳንዶቹን ለመስማት ቀርቶ ለማሰብም የሚከብድ፤ የሚያስቸግሩ ናቸው። ይህን ሐሳብ ያጠናክርልን ዘንድ የተወሰኑ ነጥቦችን ማንሳት ጠቃሚ ይመስኛል።

በዚህች ምድር ላይ ከተካሄዱ አሳዛኝ እውነታዎች / ትራጄዲዎች/ መካከል አንደኛው የዓለም ጦርነት በብዙ የሚታወስ ነው። ጦርነቱ የሰውን ልጅ እጅድ ብዙ ዋጋ ያስከፈለ፤ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ በጥቁርነቱ የሚጠቀስ ነው።

የጦርነት መነሻው እዚህ ግባ የሚባል ባይሆንም በጦርነቱ ግን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ያልተሳተፉ አገራት አልነበሩም። በዚህ ጦርነት የዓለም ህዝቦች ለሁለት ጎራ ተከፍለው በእሳት ቋያ ተለባልበዋል። ታሪክ ይቅር የማይችለው በደሎች ተፈጽመዋል።

በዚህ ብቻ አላበቃም ከጥቂት አመታት እፎይታ በኋላ ዳግም የተከሰተው ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በከፋ መልኩ ዓለምን የሰውን ልጅ ዋጋ አስከፍሏል ።

የአንደኛው ዓለም ጦርነት ተቀፅላ፤ የቂም በቀል መወጣጫ በሆነው የሁለተኛው ዓለም ጦርነትም ከአንደኛው ዓለም ጦርነት እጅግ የከፋ እና ምድር ለመሸከም የከበዳት ሁነት ተከስቶ አልፏል። በሁለተኛው የዓለም ጦርነትም በምንም ሊተካ የማይችል የሰው ሕይወት ተገብሯል፤ አጥንት ተከስክሷል፤ ደም ፈሷል።

አንዳንድ ክስተቶች በጊዜያቸው አልፈው ጠባሳቸው ግን አሁንም ድረስ የዘለቀ ነው። ለአብነት አሜሪካ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፈርጣማ ክንዷ ለማሳየት ስትል በሰው ልጅ ህሊና ፈፅሞ የማይታሰብ ድርጊት ፈፅማለች። ሄሮሽማ እና ነጋሳኪ በሚባሉ ሁለት የጃፓን ከተሞች ላይ አቶሚክ ቦንብ በማዝነብ።

ዓለም በቀደሙት ዘመናት እነዚህን ብቻ ሳይሆን በርካታ ሰው ሠራሽ አሰቃቂ መከራ እና ስቃዮችን አስተናግዳለን። ይህ ሁሉ ሲሆን ግማሹ በመንፈሳዊ መንገድ ዓለምን በእርቅና ሠላም መንገድ ሲያክም ሌላው ደግሞ እያቆሠላት፤ እያቆሰላት ዘመናትን ተሻግረናል። በመጨረሻ ግን ዓለም ለተከሰቱና ለሚከሰቱ እኩይ ተግባራት በሙሉ ይቅርታ ፍቱን መድሃኒት ሆኖ አግኝታዋለች፤ በዚህም ዛሬን ለመፈወሥ ረጅም ርቀት ሄዳለች።

ኢትዮጵያም የዚህ ዓለም አቀፍ ታሪክ አካል በመሆኗ በሦስት ሺህ ዘመን ተመሳሳይ ታሪኳ ውስጣዊ እና ውጫዊ ፈተናዎች ተጋፍጠውባታል። በውስጥ ጠላቶች ሲነሱባት፤ ከውጭ ጠላቶች ሲያሸብሯት ዛሬ ደርሳለች፤ ወደፊትም ተመሳሳይ ችግሮች እንደማያጋጥሟት ማስተማመኛ የላትም።

በታሪክ አውድ ብዙ ግራጫ ሁኔታዎችን ማለፍ ግድ ከመሆኑ አንጻር፤ ኢትዮጵያ ላለፉት ሁለት ዓመታት ያለፈችበትን ሁኔታ በቅጡ የማይረዳ ዜጋ ይኖራል ተብሎ አይታመንም። በዚህ ጦርነት ያልከፈልነው ዋጋ የለም። ከብዙ ዋጋ መክፈል በኋላም ወደ ሰላም በሚወስደው መንገድ ላይ ተገኝተናል። እሰየው የሚያሰኝ ጉዳይ ነው።

ስለ ሰላም ጥቅም ሆነ የጦርነትን አውዳሚነት ከኢትዮጵያዊ የተሻለ የሚረዳው አለ ብዬ አላምንም። የቀደሙትን የጦርነት ዘመናት ትተን ባለፉት ሁለት ዓመታት ያሳለፍነው የጦርነት ጊዜ ማየት ብቻ በራሱ በቂ ነው።

በነዚህ ቀናቶች ከፍ ላሉ ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመቶች ተዳርገናል። ስሜትና መንፈስን የሚጎዱ የጦርነትና የጥፋት ዜናዎችን ለመስማት ተገደናል። ብዙዎቻችን የዚህ አስከፊ ግዜ ማብቂያውን ረዝሞብን መጨረሻው ቅርብ እንዲሆን አጥብቅን ጸልየናል።

ከሰሞኑ በመንግስትና በሕወሓት መካከል በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የተደረሰውን ሥምምነት ተከትሎ እፎይ የሚያሰኙ ዜናዎችን እየሰማን እንገኛለን። ነገዎችንም በተሻለ ተስፋ እንድንጠብቅ የሚያስችል መነቃቃትም በውስጣችን እየተፈጠረ ነው።

ይህንን አገርን እፎይ ያስባለ ስምምነት በበጎ መንፈስ መረዳት ያልቻሉ ኃይሎች የሠላም ስምምነቱን ለማደናቀፍ በአውሮፓ እና አሜሪካ ተቀምጠው ከተቃውሞ ሰልፍ ጀምሮ ያዋጣናል ያሉትን ሁሉ እየሞከሩ ይገኛል።

እነዚህ ኃይሎች ከግጭት አካባቢዎች እርቀው ከመገኘታቸው አንጻር የሰላም ስምምነቱ ትርጉም በአግባቡ መረዳት የቻሉ አይመስሉም። በአገር ውስጥ ለምንኖር የሰላም ስምምነቱ ምን ዓይነት ያልታሰበ ሲሳይ ይዞልን እንደመጣ የተገነዘቡት አይመስሉም። ይልቁንም የጦርነት ከበሮ በመደለቅ አገርና ህዝብን ለተጨማሪ እልቂት ለመዳረግ እየተጉ ነው ።

እነዚህ ሀይሎች ወቅት እየተበቁ አንዴ የሰላም ሀዋሪያ ሌላ ጊዜ የጦርነት ሰባኪ በመሆን ወጥ ባልሆነ ስብእና እየሄዱበት ያለው የትፋት መንገድ መዳረሻው ጥፋት ስለመሆኑ ለማንም ማሰብ ለሚችል ሰው የሚደበቅ አይደለም። ግልፅም ይሁን አደባባይ የሞላው አላማቸው ይህው ነው።

እዚህ ላይ ላነሳ የፈለኩት የእነዚህ ኃይሎች የጥፋት ተልእኮ አይደለም፤ በዚህ መንገድ እየሄዱበት ካለው መንገድና መንገዱ በቀደሙት ወቅቶች እንደአገር ካስከፈለን ዋጋ አንጻር እውነታው ከሁሉም ዜጋ የተሰወረ ነው የሚል እምነት የለኝም።

ከዛ ይልቅ እኛ የጉዳዩ ባለቤቶች፤ የጥፋቱ ገፈት ቀማሾች ምን ማድረግ አለብን የሚለው ለማንሳት ነው። ለዚህ ደግሞ ዋናው ማድረግ የሚጠበቅብን ለእነዚህ አካላት ጀሯችንን በመንፈግ ለሳላም ስምምነቱ ስኬት የሚጠበቅብንን ሁሉ ማድረግ ነው። ይህን ደግሞ የምናደርገው ሥምምነቱ በእለት ተእለት ህይወት ውስጥ ያለውን ከፍ ያለ ፋይዳ በመረዳት ነው።

ከሰላም ማጣቱ ጎን ለጎን እየተፈታተነን ያለው የኖሩ ውድነት ሆነ ማህበራዊ ምስቅልቅል በአንድም ይሁን በሌላ ከጦርነቱ ጋር የተያያዘ መሆኑን በደንብ ልንገነዘብ ይገባል። የስምምነቱ ተግባራዊነት ለችግሮቹ ዋነኛ መፍትሄ መሆኑንም ማስተዋል ያስፈልጋል።

ከዚህም በላይ ለስምምነቱ ተግባራዊነት የአቅማችንን የምናደርገውም ለነገ ልጆቻችን ከእርስ በእርስ ግጭት የተላቀቀችና የበለጸገች ኢትዮጵያን የማስረከብ ታላቅ አገራዊ ኃላፊነትም ስላለብን ጭምር መሆኑን ማጤን ይገባል።

አንዳንድ አካላት የሰላም ሥምምነቱ በተደራዳሪ በመንግስት እና በሕወሓት ተወካዮች መካከል ተጀምሮ የሚያልቅ እየመሰላቸው ራሳቸውን ለጉዳዩ ሁለተኛ ወገን ሲያደርጉ ይስተዋላል። ይህ ሁኔታ ብዙ የሚያራምድ አይደለም፤ ለስምምነቱ ተፈጻሚነትም እንደ ክፍተት ሊታይ የሚገባ ነው።

እያንዳንዱ ዜጋ የአቅሙን ያህል የሠላም ስምምነቱን መደገፍ፤ ስምምነቱን የሚያደናቅፉ ተግባራትን ከመከወን መታቀብ፤ በመልሶ ማልማት ስራዎች መሳተፍ፤ ከሁሉም በላይ በማህበራዊ ሚዲያዎች ከሚደረግ የብሽሽቅ፤ የአሸናፊና ተሸናፊ ትርክት ራሱን በማቀብና ኃላፊነትን በመወጣት የሰላሙ ሂደት አንድ አካል መሆን ይጠበቅበታል።

በየትኛውም ስሌት ሁላችንንም ተጠቃሚ የሚያደርገውን ይህንን ሥምምነት አጨብጭቦ መቀበል ብቻ ሳይሆን እስከመጨረሻ ውጤታማ እንዲሆን በያለንበት ቦታ እና ሁኔታ ድጋፍ ማድረግ ይኖርብናል።

አሁን በአገራችን የተጀመረው የሠላምና የይቅርታ መንገድ እሰየው የሚያስብል ነው። የተጀመረውን የሠላም መንገድ የበለጠ ፍሬያማ እንዲሆን በኢትዮጵያዊ ጨዋነትና ሆደ ሰፊነት ሁሉም ዜጋ ኃላፊነቱን መወጣት ይጠበቅበታል።

# ነፃ ሃሳብ

# አገር እና ደጋግ ልቦች

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ዛሬ ወቅታዊውን የኑሮ ውድነት በማስመልከት ‹አገርና ታማኝ ልቦች ስል መጥቻለው። ጽሁፌን በጥያቄ መጀመር እፈልጋለው ‹ለእናተ ኢትዮጵያዊነት ምንድ ነው? በዚህ ታላቅ ጥያቄና መልስ ውስጥ ራሳችሁን አስቀምጣችሁ ተከተሉኝ። አገር የታማኝ ልቦች ነጸብራቅ ናት። ከጥንት እስከዛሬ ኢትዮጵያን የሳሉ እጆች ክፉ ሆነው አያውቁም። ኢትዮጵያን የደገፉ ክንዶች ራስ ወዳድ ሆነው አያውቅም። ኢትዮጵያዊነት ርህራሄ ነው። ዓለም ላይ ስለሌላው የሚያዝኑ ልቦች፣ ስለሌላው የሚያነቡ አይኖች ኢትዮጵያዊ ናቸው።

በዚህ ተፈጥሮአዊ ባህሪያችን ውስጥ በርካታ አስቸጋሪ የሚባሉ ጊዜአትን በጋራ አሳልፈዋል። ኢትዮጵያዊነት ሲነሳ አንድ የጋራ እውነት አለን እርሱም ተካፍሎ የመብላት ባህላችን ነው። ለናሙናነት ይሄን አነሳሁ እንጂ ኢትዮጵያዊነት ሲገለጥ አብረው የሚገለጡ በርካታ የአብሮነት ታሪኮች ያሉን ህዝቦች ነን።

ይሄ በዓለም ቀፍ ደረጃ የምንታወቅበት እሴታችን ነው። ዓለም እኔነትን ባስቀደመበት፣ ብቻ መብላትን እንደ ስልጣኔና እንደ ዘመናዊነት በያዘበት በዚህ ዘመን ላይ እኛ ኢትዮጵያዊያን ግን በጋራ በመቆም፣ በጋራ በመብላት የማንነጣጠል ህዝቦች መሆናችንን ስናሳይ ኖረናል..እያሳየንም እንገኛለን።

ይህ በየትኛውም የዓለም ክፍል ጎልቶ የማይታ የሚያኮራ ኢትዮጵያዊ መልክ ነው። ይህ ለሰው ልጅ ክብር የሰጠ፣ አንድነትን ያስቀደመ የስልጣኔ አሻራ ነው። ይህ የኢትዮጵያን ቀደምት ስልጣኔና የአብሮነት መንፈስ የሚገልጥ ሰነድ ነው።

ሁሌም እንደምለው ስልጣኔ ራስን ከመውደድና የራስን እውነት ከመቀበል የሚጀምር ነው። ሁሌም እንደምለው ዘመናዊነት ከራስ እውነት ተነስቶ ወደ ሌሎች የሚተላለፍ የአስተሳሰብ ውጤት ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ቀደምት ስልጡን ህዝቦች ስለመሆናችን በርካታ ማስረጃዎች አሉ ይሄ ሁሉ ባይሆን እንኳን አብሮ መብላታችን፣ አብሮ መቆማችን በደስታና በሀዘናችን ጊዜ መረዳዳታችን ቀዳሚነታችንን ከማሳየቱም በላይ የስልጣኔ ፈር ቀዳጆች እንደሆንን አንዱ አመላካች እውነታ ነው።

አሁንም የጥንቱን ሀያልነታችንን ይዘን እንቀጥል ዘንድ በዚህ ፈታኝ ጊዜ ላይ በመደጋገፍና በመረዳዳት አለኝታነታችንን ማሳየት ይኖርብናል። ኢትዮጵያዊነት የሚያምረው በመስጠት ነው። በመስጠት የከበረች አገር በስስት መርከስ የለባትም። አብሮ በመብላት የቆመች አገር ለኔ ብቻ በሚል ሰይጣናዊ አስተሳሰብ ልዕልናዋን ማጣት የለባትም። እንዳማረብን በአባቶቻችን የደግነት መንፈስ ወደ ፊት መጓዝ ነው የሚያዋጣን። ይህ ጊዜ በኑሮ ውድነት ህዝባችን የሚሰቃይበት ጊዜ ነው። ያለው በመስጠትና በማካፈል አጋርነቱን ሊያሳይ ይገባል።

ሰው ብዙ እውቀት፣ ብዙ ጥበብ፣ ብዙ ማስተዋል ሊኖረው ይችላል ሌላውን እንደማፍቀር፣ ለሌላው እንደ ማሰብ ግን እውቀት አይኖረውም። ሰው ብዙ በጎ ስብዕናዎች ሊኖሩት ይችላሉ አገርን እንደመውደድና ለወገን ተቆርቋሪ እንደመሆን በጎ ስብዕና አለው አልልም። ይህ የታማኝና የእውነተኛ ሰውነት መገለጫ ባህሪ ነው። አገራችን ደግሞ ከትላንት እስከዛሬ በዚህ እውነት ውስጥ የኖረች ናት።

መስጠትን የክብር ሁሉ ዘውድ፣ የጥበብ ሁሉ ምንጭ ነው። እኔ በግሌ እንደ ኢትዮጵያዊነት ጥያቄና መልስ አላውቅም..እርግጠኛ ነኝ እናንተም አታውቁም። ብዙ እውቀት፣ ብዙ ጥበብ፣ ብዙ ማስተዋል ሊኖረን ይችላል እንደ አገርና ሰው፣ እንደ ታሪክና ባህል፣ እንደ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ጥበብና ማስተዋል ግን የለንም..አይኖረንምም።

ይሄን ነው አገርና ታማኝ ልቦች ስል የማወጋችሁ። ከነገርኳችሁ በላይ የምታውቁት ሀቅ አለ? ከአገርና ሰው በላይ ምን ጥበብ ምን ልዕቀት አለ? ከዚህ እውነት በመነሳት የሰሞኑን ከኢትዮጵያ ባህልና አብሮነት ያፈነገጠውን እውነት ላውጋችሁ። የሰሞኑ የኑሮ ውድነት ያላማረረው ማነው? እርግጠኛ ነኝ ሁላችሁም ተማራችኋል። ከመማረርም ባለፈ የብዙዎቻችንን እየተፈታተነ ስለመሆኑ ሁላችንም ምስክሮች ነን። ይሄ እንዴት ሆነ? በማን ሆነ? ለምን ሆነ? ብለን ስንጠይቅ መልሱን እናገኘዋለን።

ኢትዮጵያዊነት ተካፍሎ መብላት ነው። ኢትዮጵያዊነት የታማኝ ልቦች አብራክ ነው። በዚህ እውነት ውስጥ ተወልደንና አድገን ነገር ግን በደጋግ ልቦች መሀል በበቀሉ የከፋት ልቦች የድሮ ጸዐዳ መልካችንን እያጣን ነው። ክፋትንና እኔነትን በለመዱ.. ሌብነትንና ስግብግብነትን በተማሩ አንዳንድ ነጋዴዎች የጥንት ፍቅራችንን እየተነጠቅን ነው። ራስ ተኮር የሆኑ ወጪት ሰባሪዎች ሆን ብለው የኑሮ ውድነትን በመፍጠር በህዝቡ ላይ ግፍና በደልን እየሰሩ ነው።

በተለይ ድሀው ማህበረሰብ በእነዚህ አጭበርባሪ ነጋዴዎች እየተሰቃየ ያለበት ሁኔታ ጎልቶ ይታያል። ይሄ ብቻ አይደለም የወቅቱን አስቸጋሪነት እንደ መልካም እድል በመጠቀም ድሀ አስጨንቀው በአቋራጭ ለመበልጸግ የሚሹ ኃላፊነት የማይሰማቸው ነጋዴዎች እንደ አሸን እየፈሉ ነው። ህዝብ ከማገልገል ይልቅ ያልተገባ ትርፍና ጥቅም ለማግኘት በሸቀጦች ላይ ያልተገባ የታሪፍ ጭማሬ በማድረግ ጊዜውን ፈታኝ አድርገውታል።

ምርት በመደበቅ፣ በማሸሽና ሌሎች ማጭበርበሪያ መንገዶችን በመጠቀም ከመንግስት እውቅና ውጪ በሆነ አሰራር ራሳቸውን ሲጠቅሙና ድሀ ህዝብ ሲበዘብዙ ማየት አዲስ ነገር አይደለም። ወቅታዊውን ዓለም አቀፍ ችግር እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም ሀብት ለማጋበስና የኑሮ ውድነትን በመፍጠር መንግስትና ህዝብን ሆድና ጀርባ ለማድረግ እየሰሩ ያሉ የክፋ ልቦች እዚም እዛም ተሰግስገው ይገኛሉ። የነዚህ ግለሰቦች ስውር ዓላማ የታወቀ ነው..በአንድ ላይ ሆነን እኚህን ህገ ወጦች በማጋለጥና ለህግ በማቅረብ የኑሮ ውድነቱን ማስተካከል የሁላችንም ኃላፊነት ነው።

ለዘመናት አብሯቸው የኖረን ህዝብ በማገዝና በመደገፍ በዚህ ክፉ ቀን ላይ ውለታውን እንደመመለስ ዞሮ ጨካኝ መሆን ውለታ ከመብላት ባለፈ ነውረኛ ድርጊት ነው። አብረው የማይኖሩ ይመስል..ይሄ ክፉ ቀን የማያልፍ ይመስል እንዲህ አይነት ያልተገባ ግፍ መስራት ተገቢ አይደለም። ይሄ ጊዜ ያልፋል.. ሁላችንም የምንናፍቀው አዲስ ቀን ይመጣል፤ በዚህ የንጋት ዋዜማ ላይ እንደ አባቶቻችን ስርዐት እርስ በርስ መተጋገዝ እንጂ ሆድና ጀርባ መሆን የለብንም። ይህ የኢትዮጵያዊነት መልክ አይደለም። ይህ ከአባቶቻችን የወረስነው የክብር ዘውድ አይደለም። ይህ ነውር ነው።

ይህ በሰዎች መከራ ራስን የማኖር ሰይጣናዊ እሳቤ ነው። ይህ ኢትዮጵያዊነትን የሚያደበዝዝ የራስ ወዳድነት ስብዕና ነው። በዚህ ስርዐት ውስጥ አልመጣንው። ይሄን የጭካኔ ተግባር አናውቀውም። ስርአታችን አብሮ መብላት፣ አብሮ መጠጣት ነው። ስርዐታችን ተካፍሎ መብላት ነው..ያለው ለሌለው መስጠት ነው። ስርዐታችን እንደ አብረሀም ቤት በራችንን ከፍተን ለደግነት መንገደኛ የምንጠብቅ፣ ርሀብተኛ የምናጠግብ፣ የታረዘ የምናለብስ ነው። ነውር የምናውቅ ህዝቦች ነን..ነውራችን የት ሄደ? ድሀን እንደማስጨነቅ፣ ከድሀ ላይ እንደመውሰድ ግፍና በደል፣ ሀጢያትና ነውር የለም።

ለድሀ እየሰጡ እንጂ ከድሀ እየነጠቁ ማደግና መበልጸግ የከፋ ወንጀል ነው። ለድሀ ቸርነትን እያደረጉ እንጂ በድሀ ላይ በመጨከን ነገን ማየት አይቻልም። እድገት ያለው በመስጠትና በቸርነት ውስጥ ነው። ሀብትና በረከት የሚመጣው ለድሀ ቸርነትን በማድረግ እንጂ ድሀን በማስጨነቅ አይደለም። አካሄዳችንን እናስተካክል። ስራችን በእውነትና በእውቀት ህዝብን ማዕከል ያደረገ ይሁን። እኛ ስንሰጥና ስናካፍል እንጂ ስንዘርፍና ስናታልል አልኖርንም።

እኛ በጋራ በመብላት በጋራ በመኖር እንጂ በውሸትና በማጭበርበር ራሳችንን ብቻ ስንጠቅም አልኖርንም። እኛ የሌላውን ጎደሎ በመሙላት ተያይዘን የመጣን ህዝቦች ነን ይሄን ኢትዮጵያዊ እውነት አትሳቱ። በዚህ ክፉ ጊዜ ላይ እንደ ባህላችን ለችግረኞች ልባችንን

> **ኢትዮጵያዊነት በራስ ወዳድነት የሚደበዝዝበት ሳይሆን በመስጠት የሚያብብበት ነው። ከመቼውም ጊዜ በላይ አንዳችን ለአንዳችን የምናስፈልግበት ጊዜ ላይ ነን። ወገኔ እየተራበ እኔ ጠግቤ ባድር ሰውነት ምንድነው? ጎረቤቴ ተቸግሮ እኔ ፍሪዳ ጥዬ ለብቻዬ ብደሰት እምነት ዋጋዋ ስንት ይሆናል?**

በመክፈት ይሄን ክፉ ጊዜ በጋራ መሻገር ይኖርብናል። ካልተጋገዝን የምንራመደው የብቻ መንገድ የለም። መንገዶቻችን ሁሉ በጋራ ተራምደን በጋራ የመጣንባቸው ናቸው። በእኔነት ስሜት የምንገነባው የብቻ መንገድ እኛን ከመጣል ባለፈ እርባና የለውም። እንደ አባቶቻችን በጋራ እየበላን በጋራ መኖር ነው የሚያዋጣን። እንደ አባቶቻችን በጋራ ሀሳብ የጋራ ስርዐት መገንባት ነው የሚጠቅመን።

ሰው አገር እንደሚፈልግ ሁሉ አገርም ሰው የምትፈልግበት ጊዜ አለ። አገር ሰው የምትፈልግበት ትክክለኛ ጊዜ ደግሞ አሁን ነው። ለዘመናት በአገራችን ላይ ተዘባነን ኖረናል። በህዝባችን ፍቅር ለዘመናት ታቅፈን ሳይበርደን ከትላንት ዛሬን አይተናል። አሁን ጊዜው በአንድነት መንፈስ አገር የምናቆምበትና በመረዳዳት መንፈስ ወገን የምንታደግበት ነው። ኮሮና ይዞት የመጣው ብዙ ነገር አለ። ከኮሮና ሳናገግም የሰሜኑ ጦርነት ተከሰተ። በሰሜኑ ጦርነት ተጎሳቁለን ። በዚህ ሁሉ ውስጥ ነን።

ህዝባችን ከመቼውም ጊዜ በላይ በውስጥም በውጪም በተነሱ ችግሮች በኑሮ ውድነት እየተሰቃየ ይገኛል። በዚህ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ለሚኖር ማህበረሰብ የእኛ ፍቅር፣ የእኛ ደግነት ዋጋው ምን ያክል እንደሆነ ለመገመት አይከብድም። እጆቻችን የሚሰጡበት፣ ልቦቻችን የሚያዝኑበት ሰሞን ላይ ነን። በደግነት ፈጣሪን የምናስደስትበትና የጽድቅ ስራ የምንሰራበት ሰሞን ላይ ነን። እንደ አገር ድሀ ነን፣ እንደ ህዝብ ደግሞ ችግረኛ። አዳዲስ ማህበራዊ ቀውሶች ተጨምረውብን ነገሩ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ነው። ካልተሳሰብን ይሄን ጊዜ አናልፈውም.. አዲስ የተስፋ ማለዳ እናይ ዘንድ ልቦቻችንን ለሌላው ማራራት ይኖርባቸዋል።

በኑሮ ውድነቱ ሳቢያ ወርሀዊ ደሞዛቸው የወር አስቤዛ የማይገዛላቸው፣ ቤት ኪራይ ለመክፈል ያልቻሉ ብዙ ወገኖች በዙሪያችን አሉ። መማር እየፈለጉ በብዙ ምክንያት መማር ያልቻሉ፣ መለወጥ እየፈለጉ በአቅም ማነስ ወደ ኋላ የቀሩ ብዙ ናቸው። ለነዚህ ወገኖቻችን አለኝታነታችንን ማሳየት ይጠበቅብናል። ሰው ልቡ ቀናነትን ከተላበሰ የሚሰጠው አያጣም። መስጠት ሁልጊዜ ከኪስ አውጥቶ መስጠት አይደለም። ከኪሳችን ስናጣ ከልባችን የምንሰጠው ብዙ ነገር አለ።

ከኪስ ይልቅ የልብ ስጦታ ተቀባይን ይባርካል። ኪሳችን ሲራቆት ብቻ ሳይሆን ኪሳችን በሞላ ጊዜም የልባችን ጓዳ መፈተሽ አለብን። ጊዜው ኢትዮጵያዊነት በራስ ወዳድነት የሚደበዝዝበት ሳይሆን በመስጠት የሚያብብበት ነው። ከመቼውም ጊዜ በላይ አንዳችን ለአንዳችን የምናስፈልግበት ጊዜ ላይ ነን። ወገኔ እየተራበ እኔ ጠግቤ ባድር ሰውነት ምንድነው? ጎረቤቴ ተቸግሮ እኔ ፍሪዳ ጥዬ ለብቻዬ ብደሰት እምነት ዋጋዋ ስንት ይሆናል?

እንተጋገዝ..ይሄን ክፉ ጊዜ በመተሳሰብ ማለፍ እንጂ ስር በሰደደ ራስ ወዳድነት የምንጨካከንበት አይደለም። ኢትዮጵያዊነት የተገመደበት ተካፍሎ አብሮ የመብላት ባህላችን ሊጎለብት ይገባል። ራስን ከሌሎች ማግለል ስልጣኔ አይደለም። በር ዘግቶ ለብቻ መብላት ዘመናዊነት አይደለም.. ኢትዮጵያዊነት አይፈቅድልንም። እኛ ሀበሾች ነን..አብረን በልተን አብረን የምንሞት።

ከእውነታችን እንውጣ ..ከስርዐታችሁ አንሸሽ ..አዲሱ ትውልድ ከእኛ የሚማረው ብዙ ነገር አለና መልካምነታችን ይውረሰው። በጥቂት ራስ ወዳዶች መልካችን እየወየበ ነው፣ በጥቂት ስግብግብ ነጋዴዎች አንድነታችን እየተሸረሸረ ነው። ወደቀደመ አንድነታችን፣ ወደ ቀደመ ፍቅራችን እንመለስ ዘንድ ከእኔነት እንውጣ። ያለዛ እኛም ልጆቻችንም ልንከፍለው የምንችለው አላስፈላጊ ዋጋ ከፍ ያለ ነው። ይሄ እንዳይሆን ደጋግ ልቦችን የእኛ እናድርግ።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## “የስማርት ትራፊክ” ቴክኖሎጂ የዘርፉ ችግሮች መፍትሄ ይሆን?

**ዳግም ከበደ**

በኢትዮጵያ ውስጥ ቴክኖሎጂን እንደ አንድ ችግር መፍቻ ቁልፍ የመጠቀም ባህል እያደገ መምጣቱን መረጃዎች ያሳያሉ። ከጥቂት ዓመታት በፊት ረጅም ጊዜን፣ ጉልበትን እንዲሁም ከፍተኛ መዋእለ ንዋይ የሚጠይቁ ጉዳዮች በቀላሉ በቴክኖሎጂና ዲጂታል ዘርፍ ፈጣን መፍትሄ አግኝተው መመልከት ችለናል። ከቅልጥፍና፣ አላስፈላጊ ወጪና ጉልበትን ከመቀነስ አልፎ ጥራትን የሚጨምሩ የአሰራር ስርዓቶችን በዚሁ የለውጥ ሂደት ውስጥ ማምጣት መቻሉን ነው ባለሙያዎች የሚያነሱት።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ የፋይናንስ ዘርፉና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ደረጃቸውን ማሳደግ በመቻላቸው ከላይ ያነሳናቸውን ችግሮች ማቃለል ችለዋል። የዲጂታል ኢኮኖሚ አሰራር ስርዓት፣ ከሰው ንክኪ ውጪ የሆኑ ሲስተሞች ውጤታማ እንደሆኑ የሚያሳዩ በርካታ መረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል። ቀደም ባሉት ጊዜያት በርካታ ቅሬታዎችን ሲሰማባቸው የነበሩ አንደ ባንክ አይነት ዘርፎች አሁን ቴክኖሎጂን እንደ መፍትሄ ተጠቃሚዎችን እንደየ ፍላጎታቸው እያስተናገዱ ይገኛሉ። እንዲያም ሆኖ ገና ብዙ መሻሻሎች የሚፈልጉ ጉዳዮች እንዳሉ ግን መዘንጋት የለበትም።

ኢትዮጵያ በሳይንስና ቴክኖሎጂው ዘርፍ አዲስ አብዮት ለመፍጠርና እድገቷን በዚያ ላይ ለመገንባት ቆርጣ ወደ ትግበራ ከገባች ቆይታለች። የ“ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ” ሰነድ እና ያንን እውን ለማድረግ እየተከናወኑ ያሉ ተግባሮችም ይህንኑ ነው የሚያመለክቱት። ሁሉም ቁልፍ ዘርፎች ዘመኑ የሚጠይቀውን ሳይንሳዊና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን እንዲከተሉም የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛሉ። በእርግጥ ዓለም በዘርፉ ከደረሰበት የላቀ ደረጃ አንፃር አገሪቱን ስንገመግም እጅግ ወደኋላ ከቀሩት የዓለም ክፍላት ጋር የምትመደብ መሆኗ እሙን ነው። ይሁን እንጂ ካለፉት ሶስትና አራት ዓመታት ወዲህ ተስፋ ሰጪ ጥረቶችን እየተመለከትን ነው። ለዚህም በግብርናው ዘርፍ ላይ በጎ ውጤት የሚያሳዩ የሳተላይት ቴክኖሎጂና መሰል እንቅስቃሴዎችን እንደ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል።

የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትን ማሳደግ እንደሚገባቸው ታዳጊ አገራት ከላይ ካነሳናቸው የስኬት ጅማሮዎች በተጓዳኝ ብዙ ርቀትን መጓዝ እንደሚጠበቅባቸው መገንዘብ ያስፈልጋል። በተለይ በኢትዮጵያ ውስጥ ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ችግሮችን ማቃለል ከሚገባቸው ዘርፎች መካከል የትራንስፖርትና የትራፊክ ዘርፉ ተጠቃሽ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ በተለይ ደግሞ ከፍተኛ የተሽከርካሪ ብዛት በሚገኝባት የአዲስ አበባ ከተማ ዘመኑ የፈጠራቸውን የቴክኖሎጂ ውጤቶች ተግባራዊ ባለመደረጉና ይህንን በሥራ ላይ የማዋል የግንዛቤ ክፍተት በመኖሩ ምክንያት በርካታ ችግሮች እየተፈጠሩ ይገኛሉ። ከሁሉም በላይ ግን ዘርፎቹ የሚመሩበት ዘመናዊ የአሰራር ስርአት አለመዘርጋት ከፍተኛ ተግዳሮት ሆኖ እንደቀጠለ ነው።

አይን አዲስ ንኡስ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ነች። የመኖሪያ ሰፈሯ ጀሞ አንድ ሲሆን፣ የሥራ ቦታዋ መገናኛ በልዩ ስሙ ማራቶን በሚባል አካባቢ ነው። በከተዋ የትራንስፖርት አገልግሎት ችግር ምክንያት በየጊዜው ወደ ሥራ ቦታዋና ወደ መኖሪያ አካባቢዋ ለመድረስ እንደምትቸገር ትናገራለች። ተሽከርካሪ ብታገኝም በትራፊክ መጨናነቅ ምክንያት ከአንድ ሰዓት እስከ ሁለት ሰዓት ለሚደርስ ጊዜ መቆየቷ የተለመደና የእለት ተእለት ተግባሯ እንደሆነ ትገልፃለች። የሚመለከተው የመንግሥት አካል መንገዶችን ከመስራት፣ የትራፊክ መስመሮችን በቴክኖሎጂ በመምራትና ሌሎች የመፍትሄ አማራጮችን ተጠቅሞ መፍትሄ እንዲሰጥ ትጠይቃለች።

ሌላኛው ለዝግጅት ክፍላችን አስተያየት የሚሰጠው ደግሞ የግል መኪና የሚያሽከረክረው አቶ ግርማ ፀሃይ ነው። እርሱ እንደሚለው በተለይ በአዲስ አበባ ውስጥ የትራንስፖርት ዘርፉ እና የትራፊክ እንቅስቃሴው በአግባቡ ስለማይመራ ነዋሪዎች ከሥራ ወደ መኖሪያም ሆነ ለልዩ ልዩ ጉዳዮች ወጥተው ለመግባት ይቸገራሉ። እርሱ እንደ ዋና ችግር የሚያነሳው በመንገድ ላይ በሚፈጠር ግጭት ምክንያት ተሽከርካሪዎች በቶሎ ባለመነሳታቸውና በዘመናዊ መንገድ መረጃ ሰብስቦ ውሳኔ የሚሰጥበት መንገድ ባለመኖሩ ምክንያት የመንገድ መዘጋጋት መፈጠርን ነው።

ከዚህ ባሻገር የከተማዋን የመንገድ ስርዓት የሚቆጣጠሩ ትራፊኮች መረጃን በቴክኖሎጂ አማካኝነት የመሰብሰብ ክፍተት እንዳለባቸው ማስተዋሉን ይናገራል። ከዚህ ባሻገር ትራፊኮች አሽከርካሪዎችን በህግ ጥሰት የሚቀጡበት ስርዓት ፍትሃዊነት የጎደለውና የአሰራር ክፍተት የሚታይበት እንደሆነም አስተያየቱን ይሰጣል። በኢትዮጵያ ውስጥ የትራንስፖርት ዘርፉ በርካታ መሻሻሎች እንደሚያስፈልጉት አቶ ግርማ ያምናል።

ኢንስፔክተር ዲሮ ፈከኔ በአዲስ አበባ ትራፊክ ፅህፈት ቤት የጎማ ቁጠባ ቅርንጫፍ ስምሪት ክፍል ሃላፊ ናቸው። ኢንስፔክተሩ በጉዳዩ ላይ እንደሚሉት፤ በተለይ በበአዲስ አበባ ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ አለ። ይህ ችግር ከመንገድ ጥገናና ጥበት ችግር፣ ከግጭት፣ እንዲሁም በቸልተኝነት የተከለከለ ቦታ አቁሞ ከመሄድና መሰል ችግሮች አንፃር የሚፈጠር ነው። ከዚህ ውጪ አደጋ ሲከሰት፣ አሽከርካሪዎች የደንብ ጥሰት ሲፈፅሙ፣ ስምሪት ወስደው የሚሰሩ የትራፊክ አባሎች ህግን ባልተከተለ መልኩ ደንብ ተላልፈው ሲቀጡ እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ችግሮች በትራፊክ እንቅስቃሴው ላይ እክል ይፈጠራል።

እነዚህን ችግሮች ለማቃለል በሰፊ የሰው ኃይል ስምሪትና በቴክኖሎጂ በሚታገዙ ሥራዎች እንደሚሰሩ ይናገራሉ። ከፍተኛ መጨናነቅ የሚታይባቸው ቦታዎችን ከሰው ስምሪት ባሻገር በካሜራ ታግዞ በቴክኖሎጂ ስምሪቱን ለማቃለል እንደሚሠራ ገልፀው ይህ ግን በቂ ነው የሚል እምነት እንደሌላቸው ይናገራሉ።

“ግጭት ሲፈጠር፣ የደንብ መተላለፍ ተፈጥሮ ጥፋተኞች ሲያመልጡ፣ ትራፊኮች አላግባብ አሽከርካሪዎችን ሲቀጡ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ዳኝነት መስጠት ያስፈልጋል” የሚሉት ኢንስፔክተሩ አሁን ያለው የቴክኖሎጂ ስርዓት ለችግሩ በበቂ መልኩ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አለመሆኑን ይናገራሉ። ቴክኖሎጂ የሁሉ ቁልፍ መፍቻ መሆኑን ጠቅሰው አዲስ አበባ ውስጥ ያለውን የትራፊክ ፍሰት ለመቅረፍ ዘመኑ የሚፈቅደውን ቴክኖሎጂ መጠቀም እንደሚያስፈልግ ምክረ ሃሳባቸውን ይገልፃሉ።

### ስማርት ትራፊኪንግን እንደ መፍትሄ

ሚካኤል ታዬ ይባላል። በኢትዮ ቴሌኮም የስትራቴጂክና ፕላኒንግ ሱፐርቫይዘር ነው። በሳይንስ ሙዚየም የስማርት ትራፊኪንግ ሲስተምን ካምፓኒውን ወክሎ ሲያስተዋወቅ ነበር። እርሱ እንደሚለው በሙዚየሙ ውስጥ ኢትዮ ቴሌኮም ከሚያስተዋውቃቸው ቴክኖሎጂዎች ውስጥ “ስማርት ትራፊኪንግ” አንዱ ነው።

“የምናስተዋውቅበት ምክንያት መሰል ቴክኖሎጂዎች ትላልቅ ዳታ ሴንተሮች ይፈልጋሉ። ይህ ብቻ ሳይሆን ፈጣን የሆነ የኢንተርኔት ‘5ጂና 4ጂ ኔትወርክ’ አቅርቦትም ስለሚጠይቁ ነው” የሚለው ሚካኤል፤ ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂን እውን ከማድረግ አንፃር ኢትዮ ቴሌኮም የራሱን ድርሻ ወስዶ በመስራት ላይ እንደሆነ ይናገራል።

እንደ ሚካኤል ታዬ ገለፃ “ስማርት ትራፊኪንግ” ከተለመደው የትራፊክ ክትትል፣ ቁጥጥርና ፍሰትን የማሳለጥ ሂደት ይለያል። እርሱም የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን (አርቴፊሻል ኢንተለጀንት እና አይ ኦ ቲ ዲቫይሶችን) ተጠቅሞ የሚሰራ ነው። ይህም ሰፊ የሰው ሃይል ስምሪትን፣ ጉልበትና አላስፈላጊ ወጪን ይቀንሳል። በዚህም በሰከንዶች እያንዳንዱን የትራፊክ ፍሰትና እንቅስቃሴ ያሳያል።

“ስማርት ትራፊኪንግ ቴክኖሎጂ ሴንሰር (መጠቆሚያዎችን) በግራና በቀኝ ባሉ መንገዶች ላይ ተጠቅሞ መረጃ ይሰበስባል” የሚለው ሚካኤል፣ ይህንን መረጃ ተጠቅሞ የትራፊክ መብራቱ መሄድን መፍቀድና መከልከል በየትኛው ቅፅበት መወሰን እንደሚኖርበት ለመወሰን በቀላሉ እንደሚጠቁም ይናገራል። በዚህም ከፍተኛ መጨናነቅ ያለባቸው አካባቢዎች ቅድሚያ እንዲያገኙ በማድረግ መጉላላትንና መዘግየትን እንደሚያስቀር ያስረዳል። ሌላው ይህ ቴክኖሎጂ ስማርት ስልኮች ላይ የተጫኑ መተግበሪያዎችን፣ የመንገድ ላይ ትላልቅ ቦርዶችን እንዲሁም መሰል መረጃ ማስተላለፊያ መንገዶችን ተጠቅሞ ለአሽከርካሪዎችም ሆነ ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች የተጨናነቁ መንገዶችን እንደሚጠቁም ይገልፃል። በዚህም ተጠቃሚው አማራጭ መንገዶችንና የተሻለ ፍሰት ያላቸውን መንገዶች ተጠቅሞ ያሰበበት እንዲደርስ እንደሚያግዝ ይናገራል። ይህም የትራፊክ ፍሰቱን ለሚከታተሉ ትራፊኮች እፎይታን ከመስጠቱም በላይ ጉልበትና ጊዜያቸውን ወደ ሚፈልጉ ሌሎች የክትትልና ቁጥጥር ሂደቶች እንዲጠቀሙበት እድል እንደሚሰጥ ይናገራል።

ሚካኤል ስማርት ትራፊክ ቴክኖሎጂ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች እነዚህ ብቻ እንዳልሆኑ ይናገራል። ለምሳሌ ያህል “የትራፊክ ጥሰቶች” አሊያም የህግ መተላለፎች ሲፈጠሩ ያለምንም የሰው ንክኪና ተሳትፎ በሰው ሰራሽ አስተውሎት (አርቴፊሻል ኢንተለጀንት) አማካኝነት ካሜራዎችን ተጠቅሞ መለየት እንደሚችል ይገልፃል። ይህም ማለት አንድ አሽከርካሪ ህግ ቢጥስና በስፍራው ትራፊክ ባይኖር ቴክኖሎጂው ጥፋተኛውንና አሽከርካሪውን እስከ ሙሉ መረጃው ለይቶ ለቁጥጥር ክፍል የማሳወቅ አቅም እንዳለው ይናገራል።

በተመሳሳይ አሽከርካሪው ጥፋተኛ ባይሆንና በትራፊኩ አላግባብ ቢቀጣም ይህ ቴክኖሎጂ የሰበሰበውን መረጃ ተጠቅሞ ፍትህ ማግኘት እንደሚያስችለው ይናገራል። ቴክኖሎጂው አጥፊዎችን እና የአሽከርካሪውን ባለቤት እስከነ አድራሻው መለየት የሚያስችል ቴክኖሎጂም የተገጠመለት መሆኑን ይናገራል። በአጠቃላይ ጥፋት ተብለው የተቀመጡና የተለዩ ማናቸውም የትራፊክ ህጎች በአሽከርካሪ ሲፈፀም የመለየት አቅም እንዳለው ይገልፃል።

እንደፊ ሱፐርቫይዘሩ ሚካኤል ገለፃ፤ በስማርት ትራፊኪንግ ቴክኖሎጂ አሽከርካሪዎች የተከለከለ ቦታ ቆመው የትራፊክ ፍሰቱን በሚያስተጓጉሉበት ወቅት በፍጥነት ለአሽከርካሪዎቹ በኤስ ኤም ኤስ መልእክት ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ እንዲያነሱ የሚያዝ ሲሆን በስፍራው በቸልተኝነት ሲቆዩ ግን እንዲቀጡ ያመቻቻል። ይህን መሰል ተግባር በቴክኖሎጂው ሲፈፀም “የ5ጂ” ባለ ከፍተኛ ፍጥነት ኔትወርክ የሚጠይቅ መሆኑን በመግለፅ ይህንን ኢትዮ ቴሌኮም የማቅረብ አቅም ላይ እየደረሰ መሆኑን ይናገራል።

“ቴክኖሎጂው የማዘዣ ጣቢያ አለው” የሚለው ሚካኤል፤ በዚህ ጣቢያ ከተማ ውስጥ ያሉ ሁለንም መብራቶች መቆጣጠር እንደሚችል ይገልፃል። ለምሳሌ አንድ የትራፊክ መብራት ብልሽት ቢያጋጥመውና የትራፊክ ፍሰቱ ቢስተጓጉል በመረጃ እጥረት ከጥገና ውጪ እንዳይሆን ቴክኖሎጂው ጥቆማ በመስጠት በቶሎ መፍትሄ እንዲያገኝ እንደሚያስችል ይናገራል። የተሽከርካሪ ግጭት ተከስቶ ፕላን ማንሳት ቢያስፈልግ በትራፊክ ፖሊስ የሚያስፈልገውን ረጅም ሰዓት የሚወስድ ባህላዊ አሰራር ያስቀራል። ፕላን እስኪነሳ መንገዱ ተዘግቶ መጨናነቅ እንዳይከሰትም መፍትሄ እንደሚሆን ነው ቴክኖሎጂውን እያስተዋወቀ የሚገኘው ባለሙያ የሚያስረዳው።

### እንደ መውጫ

ከተሞች ሲያድጉ የትራፊክ መጨናነቅ አብሮ ይጨምራል። ስለዚህ ባህላዊውን መንገድ ተጠቅሞ የትራፊክ ፍሰቱን ማሳለጥ አስቸጋሪ ይሆናል። የግዴታ እንደነዚህ ያሉ ቴክኖሎጂዎችን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። ቴክኖሎጂዎች ውስን የሰው ኃይል ከመጠቀማቸውም ባሻገር ትክክለኛውን መረጃ የመሰብሰብ አቅማቸው እንዲሁም ፍትሃዊ እርምጃዎችን መውሰድ መቻላቸው ተመራጭ ያደርጋቸዋል። አስፈላጊውን መረጃ በፍጥነት፣ በታማኝነት እንዲሁም በቅልጥፍና አግኝቶ በሰው ሰራሽ አስተውሎት የመረጃ መተንተን አቅም መፍትሄ ለማስቀመጥ ተመራጭ ናቸው። ቀሪውን የሰው ኃይል፣ በአነስተኛ ቁጥጥር፣ ክትትል፣ ጥገና እንዲሁም ሌሎች የስምሪት ቦታዎች ላይ በማድረግ ህብረተሰቡ በሚፈልገው ሰዓት ወጥቶ ጉዳዩን ሳይጉላላ በጊዜ ጨርሶ እንዲመለስ ማድረግ ይቻላል። ለዚህ ደግሞ ኢትዮ ቴሌኮም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መስራት ይኖርበታል።

የ5ጂ ቴክኖሎጂ አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች መዘርጋቱም “ስማርት ትራፊክ” ቴክኖሎጂን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል መሰረተ ልማት መኖሩን የሚያመላክት ነው። በመግቢያችን ላይ የዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራቸው እንግዶች አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ዘርፉ በተለያዩ ችግሮች እየተፈተነ መሆኑን አመላክተዋል። ኢትዮ ቴሌኮም የኔትወርክ መሰረተ ልማቱን ዘመኑ ወደፈቀደው ልህቀት እያደረስኩ ነው ከማለቱም ባሻገር የትራፊክ ፍሰቱን የሚያሰናክሉ ችግሮችን ይፈታል ያለውን ቴክኖሎጂ እያስተዋወቀ ይገኛል። መንግሥትና የሚመለከተው አካል የስማርት ትራፊክ ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማትን ተግባር ላይ ማዋል ቢችል የዘርፉን ማነቆዎች ይፈታ ይሆን?

## ወቅታዊ ትንታኔ

# ለሲሚንቶ እጥረት የተቀመጠው መፍትሄ ውጤታማ ወይስ ውጤት አልባ?

አስቴር ኤልያስ

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር እየጨመረ የመጣውን የሲሚንቶ ምርት ዋጋ ለማስተካከል በአገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ የሚሆን አዲስ የዋጋ ተመን ማውጣቱን ከወራት በፊት አስታውቆ ነበር። የዋጋ ተመኑ የወጣው በግብይት ሰንሰለቱ ወጥ የሆነ የንግድ ስርዓት እንዲኖር ታስቦ ሲሆን፣ ይህም ከመስከረም 5 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ለሦስት ወራት የሚቆይ መሆኑ በወቅቱ ተነግሯል።

አዲስ በወጣው የሲሚንቶ መሸጫ ዋጋ መሰረት አንድ ኩንታል ሲሚንቶ ዝቅተኛ ዋጋ 510 ብር ሲሆን ከፍተኛው ደግሞ 683 ብር ከ44 ሳንቲም ሆኖ መወሰኑም ይታወቃል። ይሁንና የወጣው የዋጋ ተመን ከነበረው ዋጋ በኩንታል በአማካይ 92 ብር ዝቅ የሚያደርገው በመሆኑ የሲሚንቶ አምራቾች ሚኒስቴሩ ያወጣውን ሲሚንቶ የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ውሳኔ ተቃውሞ ማሰማታቸው ይታወሳል።

መንግስት በሲሚንቶ አቅርቦትና ዋጋ ላይ ያለውን ችግር ለመቆጣጠርና በተለያየ ጊዜ የተለያየ መፍትሄ ለማስቀመጥ ቢጥርም እስካሁን የሲሚንቶ ዋጋ ሊረጋጋ አልቻለም። እንዳውም ከገበያ ላይ በመጥፋት የኮንትሮባንድ ንግድ ጭምር ሆኗል። የአንድ ኩንታል ሲሚንቶ ዋጋም ከአንድ ሺህ ስምንት መቶ እስከ ሁለት ሺህ ብር ድረስ በድብቅ የሚቸበቸብበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይሄ ለምን ሆነ ቀጣይ ገበያውን ለማረጋጋት መፍትሄ መሆን ያለበት ምንድነው በሚሉ እና ከዚህ ጋር ተያያዥ በሆኑት ጉዳዮች ዙሪያ ያነጋገርናቸው የቢዝነስ ባለሙያ ኢንጂነር ደሳለኝ ከበደ እንደሚናገሩት፤ የአገራችን ሲሚንቶ ችግር አሁን የመጣ አይደለም። ከሁለት ዓመት በፊት ጀምሮ ያለ እና እየተንከባለለ እዚህ የደረሰ ነው። ለዚህ አንዱ ምክንያት ላለፉት አምስትና ስድስት ዓመታት አዳዲስ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች እየተገነቡ አይደለም፤ ፋብሪካዎች አለመቋቋማቸው አንዱ የአቅርቦትና የፍላጎት አለመጣጣም እንዲፈጠር ሰበብ ሆኗል።

የአገራችን የህዝብ ቁጥር እየጨመረ በመጣ ቁጥር ቤት ሰሪውም የዚያኑ ያህል እየጨመረ መጥቷል። ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ የመንግስትም ፕሮጀክቶች እየጨመሩ መጥተዋል። ስለዚህ ይህ ሁሉ ተጠራቅሞ የሲሚንቶ እጥረት እንዲፈጠር እያደረገ ነው። ይህም ሆኖ ችግሩ በአንድ ጊዜ የመጣ አይደለም ሲሉ ይናገራሉ።

ዋናው የእጥረቱ ምክንያት የፍላጎትና አቅርቦት አለመመጣጠን ሲሆን ፍላጎትን ያጣጣመ የሲሚንቶ ምርት ወደ ገበያ እንዲገባ አለመደረጉ ነው። አሁን ባለው የኮንስትራክሽን ሂደት ባሉት ፋብሪካዎች ብቻ ፍላጎትን ማሟላት አዳጋች ነው። በቀጣይ አዳዲስ ፋብሪካዎች የማይቋቋሙ ካልሆነ መፍትሄ ማምጣትም አይቻልም ሲሉ ያስረዳሉ።

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ ከዚህ ሌላ ያሉት ፋብሪካዎች ከመቆየታቸው የተነሳ በዛው ልክ ምርታማነታቸው እየቀነሰ ይሄዳል። ያሉትም ፋብሪካዎች ማስፋፊያዎችን ሲሰሩ አይታዩም። ይህ በራሱ የሚፈለገውን ያህል ምርት ተመርቶ ለገበያ እንዳይቀርብ ስለሚያደርገው የሲሚንቶ እጥረት እንዲፈጠር ያደርጋል።

ኢንጂነር ደሳለኝ እንዳሉት ፣ ሌላው ለሲሚንቶ ምርት እጥረት ምክንያት ከተባለው ውስጥ ላለፉት ሁለት ዓመታት ያህል በአገራችን የተፈጠረው ጦርነት ነው ይላሉ፤ ለአብነትም መሶቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ የማምረት አቅሙ ትልቅ ነው። ስለዚህ የዚህ ፋብሪካ አለማምረት የሚፈጥረው ክፍተት አለ። ሌላው ደግሞ በተለያየ ምክንያት አንዳንድ የሰላም መደፍረስ በሚኖርበት አካባቢ ፋብሪካዎች ሀብታቸውን በአግባቡ መጠቀም አልቻሉም። ከዚህ የተነሳ ምርታማነታቸው ይቀንሳል። የእነዚህ ድምር ውጤት ለሲሚንቶ እጥረት ምክንያት እንደሚሆን ያመለክታሉ።

ከዚህ የተነሳ መንግስት ለሲሚንቶ እጥረት የተለያየ መፍትሔዎችን ሲሰጥ እናያለን። የሚሰጠው መፍትሄ ከተፈጠረው ችግር አንጻር የሚጠበቅ ነው። ይሁን እንጂ መፍትሔዎቹ አለመስራታቸው የሚታወቀው በየጊዜው አዳዲስ መፍትሔ በማምጣታቸው ነው። ሁሌ አዳዲስ መፍትሔ የምንሰማ ከሆነ የመጀመሪያው መፍትሔ አልሰራም ማለት ነው ይላሉ።

መንግስት መፍትሔ ብሎ አምጥቶ ያልሰራ ነው ያሉትን ኢንጂነር ደሳለኝ ሲጠቅሱ፤ አንዱ የሲሚንቶ ምርት በውስን ኤጀንቶች እንዲከፋፈል መደረጉን ነው። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ሸማቾች ከፋብሪካ በር ላይ እንዲገዙ የሚል ነው ፤ እሱም እንዲሁ መስራት አልቻለም። ከዚያም ቀጥሎ የቅዳሜና እሁድ ገበያ ተባለ፤ እሱም እንደተፈለገው ያህል መስራት አልቻለም በማለት ያስረዳሉ።

> **የሲሚንቶ እጥረቱ ዋና ምክንያት ፍላጎትና አቅርቦትን ያማከለ ምርት ወደ ገበያ እንዲገባ አለመደረጉ ነው። አሁን ባለው የኮንስትራክሽን ሂደት ባሉት ፋብሪካዎች ብቻም ፍላጎትን ማሟላት አዳጋች ነው። ስለዚህ በቀጣይ አዳዲስ ፋብሪካዎች የማይቋቋሙ ከሆነ መፍትሄ ማምጣት አይቻልም**

አሁን ደግሞ ቸርቻሪዎቹ ከገበያ ወጥተው በጅንአድ በኩል ማለትም በመንግስት አካላት በኩል እንዲከፋፈል ተደረገ፤ ይኸኛውም እየሰራ አይደለም የሚል እምነት አላቸው። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ አንደኛ ብዙ ፕሮጀክቶች ቆመዋል። ሁለተኛ ደግሞ ሲሚንቶ የሚከፋፈልበት መንገድ ለምሳሌ 15 ኩንታል ይሰጣሉ፤ ይህ የሚሰጠው አንድ ሰው እንዳለው የቤተሰብ ብዛት ነው፤ ይህ መሆን የለበትም፤ አንድ ሰው በሚሰራው ፕሮጀክት ልክ እንጂ በቤተሰብ ልክ መሆን አልነበረበትም።

ለምሳሌ የወጣው መስፈርት በቤተሰብ ደረጃ 15 ኩንታል ይላል፤ ይህ አግባብ አይደለም። ምክንያቱም ትንሽዬ ቤትም የሚሰራ 15 ኩንታል ትልቅ ፕሮጀክትም የሚሰራ 15 ኩንታል መሆን አልነበረበትም። ይህ አይነት አሰራር በሙያ የተደገፈ ቢሆንና የሚሰራውንም ፕሮጀክት አገራዊ ፋይዳ ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ቢሆን መልካም ነበር። በአሁኑ ወቅት የተጀመሩ ፕሮጀክቶች በተለይ በከተማ አካባቢ ያሉ ቆመዋል ማለት እንደሚያስደፍርም ነው ያስረዱት።

የሲሚንቶ የዋጋ ተመን መውጣቱ ይታወቃል፤ የዋጋ ተመኑ ለአንድ ወገን ብቻ ነው መፍትሔ የሚሆነው፤ አምራቾችን ከተቀመጠው ዋጋ በላይ አትሽጡ የሚል ነው። ነገር ግን እንደዛ ይቀርባል ወይ የሚለው በራሱ አጠያያቂ ነው ሲሉ ይናገራሉ። ለምሳሌ የሲሚንቶ ዋጋ ገበያ ላይ ሱቆቹ ባይኖሩም በኮንትሮባንድ አንድ ኩንታል እስከ 1 ሺ 500 እና 1 ሺ 600 ብር በድለላ እየተሸጡ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

ወይዘሮ ሳራ መኮንን የኬቲ ሮብሰን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት ማርኬቲንግ ኦፊሰር ሲሆኑ፣ ድርጅታቸው ከሚሰራቸው ተግባራት አንዱ ማዕድን ላይ መሆኑን ይናገራሉ። በቅርቡ በማዕድን ሚኒስቴር አመቻችነት በሚሊኒየም አዳራሽ በተዘጋጀው ኤክስፖ ድርጅቱ ይዞ የቀረበውም የድንጋይ ከሰል ነው። የድንጋይ ከሰሉን በአገር ውስጥ ላሉ ለሲሚንቶ ፋብሪካዎች የሚያቀርቡ ሲሆን፣ እስካሁንም ለዳንጎቴ፣ ለሙገርና ለሀበሻ ሲሚንቶ ፋብሪካዎች ማቅረብ መቻሉንም ያስረዳሉ።

እርሳቸው እንዳሉት፤ ለሲሚንቶ ፋብሪካዎቹ የሚያቀርቡት የድንጋይ ከሰል አንዋሽ ነው፤ ምርቱንም የሚያገኙት ከአርጆና ከካማሺ ነው፤ በቀጣይ ግን እሴት ጨምረው ለማቅረብና የራሳቸው የማጣሪያ ፋብሪካውም እንዲኖራቸው በመስራት ላይ ይገኛሉ። አገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት እንደመሆኗ በቀጣይ ለፋብሪካዎቹ የተሟላ የድንጋይ ከሰል ለማቅረብ ዝግጁ ናቸው። በአገራችን ደረጃ የድንጋይ ከሰል ፍላጎት ከፍ ያለ ነው። በአሁኑ ወቅት የሲሚንቶ ፋብሪካዎች የሚፈልጉት ደረጃውን የጠበቀ የድንጋይ ከሰል ነው።

ከሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ የጥራት ቁጥጥር ክፍል ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ለሲሚንቶ ምርት ዋና ግብዓት የሚባሉት የኖራ ድንጋይ፣ የሸክላ አፈርና የአሸዋ ድንጋይ ናቸው። የድንጋይ ከሰል ደግሞ በማቃጠያነት የሚያገለግል ነው። የከሰል ድንጋይ የማይገኝ ከሆነ ደግሞ ከባድ ጥቁር ናፍጣ የሚባለውን ለማቃጠያነት የሚያገለግል ይሆናል። አሁን ላይ የሙገር ፋብሪካ እየተጠቀመ ያለው የድንጋይ ከሰልን ነው።

በፋብሪካው በኩል በግብዓትነት የሚጠቀመው የኖራ ድንጋይ፣ የሸክላ አፈርና የአሸዋ ድንጋይ እጥረት የለም። አንድ የሲሚንቶ ፋብሪካ በመጀመሪያም ቢሆን የሚቋቋመው ሶስቱ ግብዓት በፋብሪካው አካባቢ በትክክልና በብዛት መኖሩ ሲረጋገጥ ነው።

ሙገር እስከ 80 በመቶ የአገር ውስጥ የድንጋይ ከሰል ከሁለት ዓመት ወዲህ መጠቀም የጀመረ ሲሆን፣ ከሃያ እስከ አርባ በመቶ አካባቢ ደግሞ ከውጭ የሚያስገባ መሆኑን መረጃ ያመለክታል። ነገር ግን የውጭ ምንዛሬ ችግር እንደዚህ እንደ አሁኑ በሚኖርበት ጊዜ የሚበረታታው የአገር ውስጡን መጠቀም ነው። ይሁንና በአገር ደረጃ የማጣሪያ ፋብሪካውም ገና ስላልተከፈተ በጅምርና በማስተዋወቅ ደረጃ ላይ ናቸው ይላል። እንደመረጃው ከሆነ፤ የድንጋይ ከሰል አቅራቢዎች ባቀረቡት ልክ ሙገር መቀበል ይችላል፤ እጥረቱም ጥራቱም ሲኖር ደግሞ ከውጭ ያስገባል። በአገራችን ነዳጅ በጨመረ ቁጥር የድንጋይ ከሰሉን ዋጋ ይጨምራል።

ከሙገር የወጣው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ ለሲሚንቶ እጥረት የሚለው ለሲሚንቶ ማምረቻ ከፍተኛ የሆኑ ማሽነሪ ያስፈልጋል። ማሽኖችን ወደአገር ውስጥ ለማስገባት ደግሞ የውጭ ምንዛሬ ያስፈልጋል። የውጭ ምንዛሬ ባጋጠመ ቁጥር ደግሞ ትልቁ ተጎጂ የሚሆኑት አምራች ፋብሪካዎች ናቸው። ምንም እንኳ ፋብሪካዎቹ ቀደም ተብለው የተቋቋሙ ቢሆኑም መለዋወጫ ስለሚፈልጉ ነው። ሌላው ደግሞ ሲሚንቶ ገበያ ላይ እንዲያጥር ከሚያደርገው መካከል ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው ያለመስራት ችግር ነው።

ለሲሚንቶ እጥረትና ለዋጋው መወደድ የተለያዩ ምክንያቶች ተጠቅሰዋል። ሆኖም ግን መፍትሄው ምን መሆን አለበት በሚል ለተነሳው ሀሳብ ኢንጂነር ደሳለኝ ይህን ብለዋል፣ «እንደመፍትሔ የሚታየኝ ፋብሪካዎቹን ማበረታታትና በተቻለ መጠን ብዙ እንዲያመርቱ ማድረግ ነው። ከዚህ ጎን ለጎንም ፋብሪካዎቹ ማስፋፊያ እንዲያደርጉ ማበረታታት ይጠቅማል። ከዚህ ውጭ ግን መፍትሄ ተብሎ የተቀመጠው የዋጋ ተመን ማውጣት ትክክለኛ ነው ብሎ መውሰድ አይቻልም »ብለዋል።

ሲሚንቶ በግብዓት እጥረት ምክንያት ሊቆም የሚችል ምርት አይደለም፤ ምክንያቱ ግብዓቱ ሁሉም እዚህ ከመሆኑ በተጨማሪ በበቂ ሁኔታ ምርቱ መኖሩ ተረጋግጦ እዛው ግብዓቱ ባለበት አካባቢ የሚቋቋም ስለሆነ በዚህ ስጋት አይኖርም፤ ነገር ግን ማቀጣጠያ የሚሆነው የድንጋይ ከሰል ወይም ጥቁር ከባድ ነዳጅን መንግስት ከውጭ ከማምጣቱ በስተቀር ሌላው በሀገር ውስጥ አለ ሲሉ ያስረዳሉ።

እርሳቸው እንዳብራሩት፤ የሲሚንቶ እጥረቱን ለመቀነስ መፍትሔው ፋብሪካዎች እንዲበረታቱና እንዲስፋፉ ማድረግ ነው። ለምሳሌ የዛሬ 10 ዓመት አካባቢ የሲሚንቶ ችግር እንዲፈታ ተብለው የተተከሉ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ነበሩ። በስድስት ወር ውስጥ አነስተኛ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ሊተከሉ ይችላሉ፤ ለምሳሌ ደጀን በዚያን ጊዜ ችግሩን ለመቋቋም ተብሎ ሁለት የዳንጎቴ የመጀመሪያዎቹ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ተተክለው ነበር፤ አሁን ይህ ችግር እያለ እንኳን አገልግሎት የሚሰጡ አይደሉም፤ ቆመዋል። ከዚህ ሌላ ሙከ ጡሪ አካባቢም እንዲሁም ቆቃ አካባቢም አለ፤ እነዚህ አነስተኛ ፋብሪካዎች ናቸው፤ አሁን ግን አይሰሩም፤ ቆመዋል። ምክንያታቸው ምን እንደሆነ ባላውቅም መንግስት ትኩረት ሰጥቶ እነዚህ አነስተኛ የሆኑ ፋብሪካዎች እንዲሰሩ ቢደረግ ፤ እንዲሁም እንደእነሱ አይነት አነስተኛ የሆኑ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በየቦታው ቢኖሩ ሲሚንቶን ከአንዱ ወደሌላ ቦታ ከማጓጓዝም ጭምር የሚያድኑ ይሆኑ ነበር።

ሌላ መፍትሔ ነው ብለው የተናገሩት፤ ለምሳሌ ኮንክሪት የተባለውን አርማታ ለመሙላት ሰው በየቦታው ጠጠር ዘርግፎ አሸዋ እያደረገ ነው የሚያመርተው፤ ነገር ግን ኮንክሪት (አርማታ) የሚያምርቱና የሚሸጡ ድርጅቶች አሉ። እነሱ በተፈለገ ሰዓት ማምጣት ይችላሉና አንድ የኮንስትራክሽን ኩባንያ ሲሚንቶን የግድ መግዛት አይጠበቅበትም፤ ስለዚህ ይህንንም አማራጭ ማየቱ ተገቢ ነው። ሰሞኑን እንዲያውም የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ባለድርሻዎችን በማሰባሰብ እነርሱን ሲያበረታታ ነበር። እነርሱን ማበረታታት ከኮንትሮባንድ ያድናል።

አሁን ያሉት ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው እያመረቱ ነው ማለት አንችልም፤ ምክንያቱም ለምሳሌ ሙገር ለተወሰነ ጊዜ እያመረተ የነበረው በጣም በጥቂቱ ነበር። ጥሬ እቃውን የሚያገኝበት ቦታ ስላልነበር ከዛ ጋር በተያያዘ ችግር ነበር፤ ነገር ግን ሰላሙ ሲመለስ ወደማምረት ገብቷል። ይሁንና ችግሩ ሲሚንቶ ፈላጊው ብዙ በመሆኑ አሁንም ቢሆን በተፈለገው ልክ ማግኘት እየተቻለ አይደለም ብለዋል።

የመጨረሻ መፍትሄ ነው የምለው ይላሉ ኢንጂነሩ፣ ብዙ ሲሚንቶ ማምረት ነው። ያሉት ሲሚንቶ ፋብሪካዎች ላይ ብቻ ከተወሰንን ምርት አይኖረንም፤ ስለዚህ በአገራችን ትልልቅ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ሊኖሩን የግድ ነው። አሁን መሰረት የተጣለባቸው የሲሚንቶ ፋብሪካዎች አሉ። ለምሳሌ አንድ ድሬዳዋ ሌላው ለሚ አካባቢም የናሽናል ሲሚንቶ ተጀምሯል። ይህኛው የሶስት ሲሚንቶ ፋብሪካዎች ያህል ሊያመርት የሚችል ነው።

መንግስት ለግብርናው በተለይም ለስንዴ ትኩረት እንደተሰጠው ሁሉ ብዙ ሲሚንቶ እንዲመረት ለዘርፉ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። ባለሀብቶችን እየደገፉ ወደማምረት እንዲመጡ ማድረግ ችግሩን ለመቅረፍ ያግዛል። አሁን በመንግስት የተቀመጠው የዋጋ ተመን ብቻውን መፍትሄ አይሆንም። ስለዚህ ጎን ለጎን ስራዎች መስራት ያስፈልጋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# የፆታ እኩልነት ክፍተት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

አስናቀ ፀጋዬ

ዛሬ ላይ ለመድረስ በሴትነቷ በርካታ ፈተናዎችን አልፋለች። ሆኖም የገጠሟትን ፈተናዎች በራሷ ጥረት ታግላ ዛሬ ላይ በኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ከሚያስተምሩ ምሁራን መካከል አንዷ ለመሆን በቅታለች።

ስሟ ዶክተር ትርሲት ሳህለድንግል ይባላል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ተመራማሪ፣ በሶሻል አንትሮፖሎጂ ትምህርት ክፍል መምህር እና በቅርቡ በዚሁ የትምህርት መስክ የፒኤች ዲ ዲግሪ ባለቤት ሆናለች። ላለፉት ጥቂት አመታትም ስትማርና ስታስተምር ቆይታለች።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪ እያለች በእርሷም ሆነ ሌሎች ከእርሷ ጋር ሲማሩ በነበሩ ሴት ተማሪዎች ላይ በተለያየ መልኩ ፆታዊ ጥቃት ሲደርስ እንደነበር ታስታውሳለች። በጊዜው በሴት ተማሪዎች ላይ ፆታዊ ጥቃት ሲደርስ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማድረጉ ተግባር ደካማ እንደነበረም ትገልፃለች። በሴቶችና ወንዶች መካከል የፆታ እኩልነት እንደሌለም ታስረዳለች።

ዩኒቨርሲቲዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉና የማህበረሰቡ ነፀብራቅ በመሆናቸው በነዚህ ተቋማት የፆታ እኩልነት አለመኖር አዲስ እንዳልሆነም ነው ዶክተር ትርሲት የምትናገረው። ይህ ችግር እንዲሚቀጥልና ከዚህም በላይ ገፍቶ ሊሄድ እንደሚችልም ትጠቁማለች።

መጀመሪያ አካባቢ በምንም አይነት መልኩ የሴቶች የፆታ እኩልነት ጥያቄ የማይመለስ እንደነበር፤ ነገር ግን አሁን በተደረጉ ትግሎች እየተሻሻሉ የመጡ ነገሮች እንዳሉ ትገልፃለች። እርሷ አሁን የደረሰችበት ደረጃም ለዚህ አንዱ ማሳያ ሊሆን እንደሚችልም ትጠቅሳለች።

በተለይ ሴቶች መማራቸውና የትምህርት ደረጃቸው እየጨመረ መምጣቱ የትግሉ ውጤት መሆኑንም ታስባለች። ነገር ግን አሁንም ችግሩ ቀጥሎ በዩኒቨርሲቲዎችም ሆነ በሌሎች ተቋማት ውስጥ እንዳለ ነው የምትገልጸው። ይህም በተለያየ መንገድ ሊገለፅ እንደሚችልም ትጠቁማለች።

‹‹ለሴቶች ምቹ ሁኔታ የለም የምትለው›› ዶክተር ትርሲት እርሷ ከአስር ዓመት በፊት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ስትቀጠር በምን መልኩ ማስተማርና ከዩኒቨርሲቲው ሁኔታ ጋር አብራ መሄድ እንዳለባት አንድም የነገራት ሰው እንዳልነበር ታስታውሳለች። ከሌሎች የዩኒቨርሲቲው ወንድ መምህራን ጋር የነበራት ግንኙነትም የከረረ በመሆኑ ይህ ለሷ ከባድ ውጣውረድ እንደነበረም ነው የምታስታውሰው።

ተማሪዎቿ በሆነ አጋጣሚ ስልኳን አግኝተው እየደወሉ የመጀንጀን ነገሮች እንደነበሩም ትገልፃለች። እርሷ ያለፈችበትን ሁኔታ ላለመድገም ከተማሪዎች ጋር እንደ ጓደኛ የመሆን መርህ የነበራት ቢሆንም በተለይ የተማሪዎች ውጤት ሲደርስ የነበረውን ውጣ ውረድ መቋቋም አቅቷት እንደበረም ነው የምትገልጸው። አልፈው የሚመጡ ሰዎች እንዳጋጣሚትም ትናገራለች።

እንደውም በአንድ ወቅት አንዱ ተማሪዋ ታክሲ ውስጥ ስትገባ አይቷት ተከትሎ ገብቶ በግድ የፍቅር ጥያቄ እንዳቀረበላት ታስታውሳለች። እነዚህንና መሰል የፆታ ትንኮሳዎች ከወንድ ተማሪዎቿ ሲገጥሟት እንደነበርም ገልፃ፤ እንዲህ አይነቱ ችግር ሲገጥም ችግሩን እንዴት ማለፍ እንዳለባት የሚያሳዩ ከእርሷ የበለጠ ልምድ ያላቸው መምህራን እንዳልነበሩም ታመለክታለች።

ዶክተር ትርሲት እንደምትናገረው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በተለይ ከሴት መምህራን ጋር አብሮ መስራት፣ መደጋገፍና ሴቶች ፆታዊ ጥቃት እንዳይደርስባቸው መከላከልና ቢደርስባቸው እንኳን የገጠማቸውን ችግሮች እንዴት ማለፍ እንደሚችሉ ሀሳብ ማቀበል ላይ ሰፊ ክፍተት ይታያል።

የአካዳሚው አካባቢ ሁሌም ማንበብና ውጥረት የሚታይበት እንደመሆኑና ብዙ ነገር እንደመፈለጉ ለዚህ የግድ መተጋገዝ የሚጠይቅ ቢሆንም ይህ ነገር ግን በብዙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ እምብዛም አይታይም። በጀማሪና ልምድ ባላቸው መምህራን መካከልም ሰፊ ክፍተት እንዳለ ሁኔታዎች ያሳያሉ። ተነጋግሮ ችግሮችን የመፍታትና የመረዳዳት ባህሉም ዝቅተኛ ነው።


ዶክተር ትርሲት ሳህለድንግል፣


ዶክተር ሰዋለም ፀጋ፣

ፎቶ፡- በአስናቀ ፀጋዬ፣

እንደ ዶክተር ትርሲት ገለፃ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ያለውን የፆታ እኩልነት ክፍተት ለመሙላት ከሁሉ በፊት ተቀራርቦ መስራት ያስፈልጋል። መገፋፋት ባለ ቁጥር በርካታ ነገሮች ሊጎሉ ስለሚችሉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሰው ልጆች ጭንቅላት የሚሰራባቸው በመሆኑ መልካም ስብእና ግንባታ ላይ ብዙ ሊሰራ ይገባል።

ይህ በሆነ ቁጥር ሰዎች ሌላውን እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው ያውቃሉ። ጥሩ የመግባባት ክህሎት ማዳበርም ያስፈልጋል። ሁሌም አምባገነን መሆንና ሁሌም እውቀቱ መምህራኑ ጋር ብቻ እንዳለ መቁጠርም አያስፈልግም። ከዚህ ይልቅ ሌሎችንም መስማት ተገቢ መሆኑን መረዳት ይገባል። የሁለትዮሽ እውቀት መጋራትም ያስፈልጋል።

ብዙ ጊዜ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከላይ ወደታች ናቸው። ሌላው ምንም አያቅም ብለው ነው የሚነሱት። የትኛውንም ሴክተር መምራት ይፈልጋሉ። ይህ ግን መሆን የለበትም። ዩኒቨርሲቲዎች ራሳቸው ከማህበረሰቡና ከሌሎች ሴክተሮች መማር አለባቸው። አሁን እየተወራ ላለው የትምህርት ጥራት መጓደልና ውድቀት ብሎም የማህበረሰብ ክስረት ዩኒቨርሲቲዎች ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ። አሁን ላይ ለተፈጠሩ ቀወሶችም በጎ ባልሆነ መልኩ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

ከዚህ አንፃር ይህን ክፍተት መቀበል ለማስተካከል ጠቃሚ ይሆናል። በተለይ ለወደፊት የተሻለ ነገር ለማምጣት ፖሊሲን ብቻ ሳይሆን የሰዎችን ጭንቅላትን ጭምር መቀየር ያስፈልጋል። መልካም ስብእና ግንባታና መደጋገፍ ላይም መስራት ይገባል።

ከዚህ በፊት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ሴቶች መብታቸውና ግዴታቸው ምን እንደሆነና ፆታዊ ጥቃት ሲደርስባቸው ብሎም በሴትነታቸው ችግሮች ሲያጋጥሟቸው የት መሄድ እንዳለባቸው የተለያዩ ኔትዎርኮች ነበሩ። ሆኖም ይህ ኔትዎርክ በመላላቱ ምክንያት መምህራን ከሚያደርጓቸው መጠነኛ ጥረቶች ውጭ ስርዓቱን የተከተለ ስራ እየተሰራ አይደለም። በዚህ ጉዳይ ላይ ራሱን ችሎ የተቋቋመ ቢሮም የለም።

ከዚህ አንፃር በርካታ ክፍተቶች በመኖራቸው በብዙ ሊሰራ ይገባል። በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ያሉ አመራሮች ችግሩን ወርደው ማየት ይጠበቅባቸዋል። ጉዳዩን ፖለቲካዊ መልክ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ በፀዳ መልኩ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ተገቢ ነው።

ዶክተር ሰውዓለም ፀጋ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሳይኮሎጂ ትምህርት ቤት ተባባሪ ፕሮፌሰርና በስርዓተ ፆታና ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከል ዳይሬክተር ሆነው ይሰራሉ። እርሳቸው እንደሚሉት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሶስት ዋና ዋና ዘርፎች ስራቸውን ይሰራሉ። እነዚህም ማስተማር፣ መመራመርና ማህበራዊ አገልግሎት መስጠት ናቸው።

ከዚህ አኳያ በሶስቱም ምሶሶዎች በማስተማር የፆታ ጥናት በሚል ትምህርቱ ሊሰጥ ይችላል። በምርምር ደግሞ የተለያዩ ችግር ፈቺ ጥናቶችን ያደርጋሉ። በማህበራዊ አገልግሎትም ከሲቪል ሰርቪስ ድርጅቶችና ከማህበረሰቡ ጋር የማስተማር፣ የአድቮኬሲና ሚዲያውን በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ይሰራሉ።

የፆታ እኩልነትን ከማረጋገጥ አንፃርም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሚናቸው ጉልህ ነው። ነገር ግን ተቋማቱ ሚናቸውን በሚፈለገው ልክ ባለመወጣታቸው የፆታ እኩልነትን በሚገባ ማረጋገጥ አልተቻለም። ይህ ሲባል ግን ደግሞ የፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ በተቋማቱ በኩል ምንም አልተሰራም ማለት አይደለም።

ዶክተር ሰውዓለም እንደሚያብራሩት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሚናቸውን በሚገባ በመወጣት የፆታ እኩልነትን እንዲያረጋግጡ ሚዲያውን በአግባቡ ሊጠቀሙበት ይገባል። ስርዓተ ፆታ ላይ ያተኮሩ ጥናትና ምርምሮችን መስራትም ይጠበቅባቸዋል። በተለይ የፆታ ጉዳይ ሁሉንም የትምህርት መስኮች የሚነካ በመሆኑ ተቋማቱ የስርዓተ ፆታ ጉዳይን ከነዚህ የትምህርት መስኮች ጋር አዛምደው ጥናትና ምርምሮችን መስራት ይጠበቅባቸዋል።

ተቋማቱ ያጠኗቸውን ጥናቶች ደግሞ ሼልፍ ላይ ማስቀመጥ ብቻ ሳይሆን ማሳተምና ማሰራጨት፣ በሚዲያ ማቅረብ፣ ሀገር እንዲያውቀውና ህዝብ እንዲማርበት ማድረግ ይኖርባቸዋል። በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ሴቶች ደግሞ ሞዴል ሆነው በሚዲያ ሲቀርቡ በየቤቱ ያሉ ታዳጊ ሴቶች ይነሳሳሉ። በሂደት የሴቶች እኩልነት ሲረጋገጥና የበለጠ እየተዋወቀ ሲሄድ ሀገር ታድጋለች። ሀገር እንድታድግ ደግሞ ተባብሮ መስራት ከሁሉም ይጠበቃል።

የኢትዮጵያ ስርዓተ ፆታ ፖሊሲ እ.ኤ.አ በ2015 ወጥቷል። በመቀጠልም ተከልሷል። የትገባራ መመሪያም ተዘጋጅቶለታል። ፖሊሲውን ተከትሎ ቀደም ሲል ከነበረው ሁኔታ አንፃር አሁን ላይ ብዙ መሻሻሎች ይታያሉ። ለአብነትም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሁለት ሴት ምክትል ፕሬዝዳንቶች አሉ። ቀደም ሲል ሴት ዳይሬክተሮችም በቁጥር አነስተኛ የነበሩ ቢሆንም አሁን ላይ ቁጥራቸው አድጓል። የዲኖችም ቁጥር ከፍ ብሏል።

ይህ ለውጥ ታዲያ በስርዓተ ፆታ ፖሊሲው መሻሻል ምክንያት ነው የመጣው ወይስ በሌላ የሚለው ጉዳይ ግን ጥናት ይፈልጋል። ነገር ግን ከስርዓተ ፆታ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ለውጦች አሉ። ሆኖም ለውጦቹ በቂ ባለመሆናቸው ከዚህም በላይ ብዙ መስራትን ይጠይቃል።

ዩኒቨርሲቲዎች የፆታ እኩልነት ትንሹን ችግር ነው የሚያሳዩት። ከዚህ አንፃር ከዩኒቨርሲቲዎች ባሻገር በመላው ሀገሪቱ የፆታ እኩልነት ችግር አለ። በመሆኑም ከዩኒቨርሲቲዎች በዘለለ ከፆታ እኩልነት ጋር በተያያዘ በየትኛውም ቦታ ሄዶ መስራት የግድ ይላል። ዩኒቨርሲቲዎችም የማህበረሰብ አገልግሎት አንዱ ስራቸው ነውና ማህበረሰቡ ውስጥ ገብተው የፆታ እኩልነት ችግሮችን ነቅሰው በማውጣት ለውጥ እንዲመጣ መታገል ይጠበቅባቸዋል።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**በ1952 ከወጡት የአዲስ ዘመን ጋዜጦች በማኅበራዊ ጉዳይ ላይ ያተኮሩ ዜናዎችን መርጠናል። የግዮን መዋኛ ገንዳ መመረቅ ዜና ስናየው በዘመናችን ለሸገር ልጆች መዋኛ መዝናኛ ለምን የሳቸውም እንሳለን። በፍቼ ከተማ ቀን ቀን የኑግ ዘይት እያመረቱ የነበሩ ባለሀብቶች ሌሊት ለከተማው ነዋሪ ኤሌክትሪክ ብርሃን ያዳርሱ ነበር። ሌሎችም ዜናዎች አሉ እነሆ።**

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

### በሁለት ቀን ሦስት ልጆች

በወለጋ ጠቅላይ ግዛት በጉድሩ አውራጃ በጐበያ ም/ወረዳ ግዛት በግራዝማች አመኑ መልከኘት ውስጥ የምትገኝ የአቶ ደሬሳ ወዬሳ ባለቤት የሆነች እመት አሠጋሽ ምስክር የተባለች በወላድነቷ የታወቀች ሴት መስከረም ፲፫ ቀን ፶፪ ዓ ም አንድ ወንድ ልጅ ከወለደች በኋላ እንደገና በሦስተኛው ቀን ማለት መስከረም ፲፭ ቀን ፶፪ ዓ ም አንድ ወንድ ልጅና አንዲት ሴት ልጅ ወልዳች ። በጠቅላላው ሦስት ልጆች በመውለዷ ሀገሯን የምታኮራ መሆኑ ቢታወቅም ፤ ለጊዜው የሚደርስባትን የዕለት ሁኔታ ሁላችንም ልናውቅላትና ልናዝንላት ይገባናል። ይህንንም ሁኔታ ለማወቅ የቻልነው የክፍሉ ወረዳ ዋና ጸሐፊ አቶ ጳውሎስ ለአውራጃው ገዥ ለተከበሩ ደጃዝማች ተስፋዬ ወልዴ በቁጥር ፩፻፴፩/፴፮ መስከረም ፳፯ ቀን ፶፪ ዓ ም ሲጽፉ ባደረጉልን ግልባጭ ስለሆነ፤ የነገሩ እርግጠኝነት የሚታመን ነው።

የሕፃናቱ ማደግ ያለማደግ የሚታወቀው የፈጠራቸው ብቻ መሆኑን ከተገነዘብን በኋላ፤ ፅንሳቸው ወይም ዘራቸው እንዴት ነው? የማለት ሀሳብ ይታገለን ይሆናል።

የወለጋ ጠቅላይ ግዛት አዣንስ ኃይለመስቀል ወልደየስ

**(በኅዳር 29 ቀን 19 52 ከወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)**

### የአዲሱ የውሀ መዋኛ መመረቅ

መስከረም ፳፱ ቀን ፲፱፻፶፪ ዓ. ም ከዕኩለ ቀን በላይ በ፱ ሰዓት በግዮን ሆቴል ቅጽር ግቢ ውስጥ አዲስ የተሠራ የውሀ መዋኛ ሥፍራ በልዑል ሣህለ ሥላሴ ኃይለሥላሴ የገሙ ጎፋ ጠቅላይ ግዛት አስተዳዳሪ ተመርቆ ተከፍቷል።

በአመራረቁ ሥነ ሥርዓት ላይ ንጉሣውያን ቤተ ሰብ፤ ክቡራን ሚኒስትሮችና መኳንንት፤ እንዲሁም የውጭ ሀገር መንግሥታት እንደራሴዎች ተገኝተው ነበር።

የአዲሱ መዋኛ አካባቢ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማና በልዩ ልዩ ኅብረ ቀለማት ባላቸው ጌጣ ጌጦች አምሮና አሸብርቆ ከመገኘቱም በላይ፤ በብዙ መቶ የሚቆጠር ሕዝብ ወደ በዓሉ ሥፍራ ሔዶ የአመራረቁን ሥነ ሥርዓት ተመልክቷል።

ልክ ፱ ሰዓት ሲሆን፤ ልዑል ሣህለ ሥላሴ ደርሰው በተዘጋጀላቸው ሥፍራ ላይ እንደተቀመጡ ስድስት ዋናተኞች ከአምስት ሜትር ርቀት ላይ እየዘለሉ ወደ ተከተረው ውሀ በመጥለቅ፤ የአጠላለቅ ዋና አሳዩ።

**(ጥቅምት1 ቀን 1952 ከወጣው አዲስ ዘመን)**

### ኃይለኛ አውሎ ነፋስ

በኅዳር ፲፯ ቀንና ፲፰ ቀን በአሩሲ ጠቅላይ ግዛት በአሰላ ከተማ ኃይለኛ አውሎ ነፋስ ስለተነሳ የብዙ ቤት ቆርቆሮዎችን በሙሉ ሳይሆን በከፊል እያነሳ አውልብልቧቸዋል። እንደዚሁም ብዙ ሊባል አይቻልም እንጂ አነስተኛ ዛፎችንም ጥሏል።

በሌላ በኩል ምንም ጉዳት ያደረገው ነገር የለም።

• • •

### ዝናብ

ኅዳር ፳፩ ቀን ፶፪ ዓ ም ጀምሮ በአሰላ አካባቢ ከፍ ያለ ዝናብ ስለዘነበ በመሰብሰብ ላይ ለሚገኘው አዝመራ ሳያሰጋ አይቀርም በማለት ገበሬዎች የስጋት መንፈስ አድሮባቸዋል።

አንዳንዶቹም ጨረቃዋ ጠፍ በመሆንዋ ጥቂት ጊዜ ነው እንጂ ብዙ አይዘንምም በማለት ቀድሞ ምልክት ሲናገሩ አንዳንዶች ደግሞ ለማናቸውም ሰብልን ቶሎ ቶሎ መሰብሰብ አይከፋም ሲሉ ይሰማሉ።

**የአሩሲ ጠቅላይ ግዛት አዣንስ ተፈራ አሸናፊ።**

### የኤሌክትሪክ ብርሃን መስፋፋት

የፍቼ ከተማ ብዙውን ጊዜ የኤሌክትሪክ ብርሃን እንዳልነበረው የታወቀ ሲሆን ከሐምሌ ፲፱፻፶፪ ዓ. ም ወዲህ በፍቼ ከተማ የሚገኙት ያኑሪስ ወንድማማቾች ነጋዴዎች ባለ ፳፬ የፈረስ ጉልበት ሞተር አቋቁመው በሥራ ሰዓት የኑግ ዘይት ሲያወጣ የምሽቱን ጊዜ ግን ለከተማው ሕዝብ የኤሌክትሪክ ብርሃን በመስጠት የንግድና የመኖሪያ ቤቶችን በብዙ እንደጠቀመ አንዘነጋውም።

ነገር ግን የሞተሩ ኃይል ከተማውን በሙሉ በኤሌክትሪክ ብርሃን ለማገልገል ስላልቻለ እነዚሁ ወንድማማቾች በከተማው መካከል የነበረውን ሞተር አንስተው ከከተማው መግቢያ በር ላይ ፲፭ ሜትር በ ፲፭ በሠሩት መጋዘን ውስጥ ባለ ፹ ፈረስ ጉልበት የዘይት ማውጫ ሞተር አቋቁመው የኑጉ ዘይት በትሩ መልክና መአዛ እየወጣ ገበያውን ከማስፋፋቱም በላይ ፳፬ ሰዓት ሙሉ ባለማቋረጥ የኤሌክትሪክ ብርሃኑን የሚሰጥ ሆኗል። ካሁኑ በፊት የኤሌክትሪክ ብርሃን ያላገኙትም ቦታዎች ሁሉ እንዲታደላቸው ምሶሶውን በማቆምና ሽቦውን በመዘርጋት ሥራ ላይ ስላሉ ከፍተኛ ብርሃን ያለውን ኤሌክትሪክ የፍቼ ከተማ ነዋሪ ሕዝብ በሙሉ ለማግኘት ችሏል።

የመርሐ ቤቴና የሰላሌ አውራጃ አዣንስ ላዕከ ደስታ

**(ኅዳር 4 ቀን 19 52 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን )**

# ዓለም አቀፍ

## በቱርክ በተፈጸመ ጥቃት 6 ሰዎች ተገደሉ



በቱርክ ኢንስታንቡል መሃል ከተማ በተፈጸመ “የሽብር” ጥቃት 6 ሰዎች መገደላቸውን እና 81 ሰዎች መቁሰላቸውን የአገሪቱ ባለስልጣናት አስታወቁ።

እሁድ እለት በቱርክ ታክሲም ስኩዌር ተብሎ በሚጠራው የገበያ ስፍራ የተከሰተውና ለሕይወት መጥፋት ምክንያት የሆነው የቦምብ ፍንዳታ በሴት መፈጸሙን የአገሪቱ ምክትል ፕሬዝዳንት ፉአት ኦክታይ ተናግረዋል።

የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚንስትሩ ደግሞ ቦንቡን በማስቀመጥ የተጠረጠረ ሰው በፖሊስ ቁጥጥር ሥር መግባቱን ገልጸው፤ ለፍንዳታው የኩርዲስታን ሠራተኞች ፓርቲን (ፒኬኬ) ተጠያቂ አድርገዋል።

ከጥቃቱ በኋላ መግለጫ የሰጡት ፕሬዝዳንት ረሲፕ ታይፕ ኤርዶሃን ፍንዳታውን በማውገዝ ጥፋተኛው እንደሚቀጣ ገልጸው፤ የሽብር ጥቃት በከተማዋ ሊፈጸም እንደሚችል ምልክቶች እንደነበሩም አውስተዋል።

የፍትሕ ሚንስትሩ ቤኪር ቦዛዳግ ደግሞ ፍንዳታው ባገጠመበት ቦታ አንዲት ሴት ለ40 ደቂቃዎች ከተቀመጠችበት ቦታ እንደተነሳች ፍንዳታ ማጋጠሙን ጠቅሰው፤ ፒኬኬ የተሰኘው የሚሊሻ ቡድን ከቱርክ ግዛት ላይ ነጻ የኩርዲሽ አስተዳደር ለመመስረት ይፋለማል። ቱርክ፣ የአውሮፓ ሕብረት እና አሜሪካ ይህን ቡድን አሸባሪ ሲሉ ፈርጀውታል።

ፍንዳታው ወዳጋጠመበት ቦታ ያቀናቸው የቢቢሲ ጋዜጠኛ በአካባቢው በርካታ የፖሊስ አባላት መሰማራታቸውን፣ ሄሊኮፍተሮች አካባቢውን ከላይ ሆነው ሲቃኙ እና በርካታ ቁጥር ያላቸው አምቡላንሶች ደግሞ በስፍራው ሲመላለሱ ተመልክታለች።

ፍንዳታው ባገጠመበት ቦታ የነበረች አንድ የዓይን እማኝ፤ “ሰዎች ሲሯሯጡ እና በነበርኩበት ካፌ በኩል ወደ ሆስፒታል የሚሄዱ ብዙ የተጎዱ ሰዎች አይቻለሁ” ብላለች።

ፍንዳታው ካጋጠመበት 50 ሜትር ርቆ የነበረው ሴማለ ዱኒዘሲ ለኤኤፍፒ ሲናገር፤ “ጥቁር ጭስ ነበር። የፍንዳታው ድምጽ በጣም ከባድ ከመሆኑ የተነሳ ጆሮ የሚደፍን ነበር” ብሏል።

በቱርክ ያልተለመደ የተባለው ጥቃት ከተሰነዘረ በኋላ በርካታ አገራት ከቱርክ ጎን እንደሚቆሙ መልዕክት እያስተላለፉ ነው።

አሜሪካ ከሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን ድርጅት (ኔቶ) አባል አገሯ ቱርክ ጋር በጸረ-ሽብር ዘመቻ እንደምትተባበር ገልጻለች።

የፈረንሳይ ፕሬዝዳንት ኢማኑኤል ማክሮን በትዊተር ገጻቸው ላይ በቱርክ ቋንቋ፤ “ሕመማችሁን እንጋራለን በሽብር ላይ በሚደረገው ትግል አብረናችሁ አለን” ብለዋል።

የዩክሬን ፕሬዝዳንት ቮሎድሚየር ዜሌንስኪ በተመሳሳይ በተርኪሽ ቋንቋ፤ “ወዳጅ የሆነው የቱርክ ሕዝብ ህመም እኛንም ይሰማናል” ብለዋል።ፓኪስታን፣ ጣሊያን እና ግሪክ በተመሳሳይ ጥቃቱን ተከትሎ ለቱርክ አጋርነታቸውን የገለጹ አገራት ናቸው።





## ጆ ባይደን እና ዢ ጂንፒንግዢ በኢንዶኔዥያ ሊገናኙ ነው

የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን እና የቻይናው ፕሬዚዳንት ዢ ጂንፒንግዢ በኢንዶኔዥያ ተገናኝተው ወሳኝ ጉዳዮች እንደሚነጋገሩ ይጠበቃል።

ሁለቱ መሪዎች ለመጨረሻ ጊዜ በአካል የተገናኙት በኦባማ አስተዳደር ወቅት ባይደን ምክትል ፕሬዝዳንት በነበሩበት ወቅት ነው

ውይይቱ በዋይት ሀውስ በሁለቱ ልዕለ ኃያላን ሀገራት መካከል የተካረረውን ግንኙነት መፍትሄ ያስቀምጣል የሚል ተስፋ ተሰንቋል።

ሁለቱ መሪዎች ከቡድን 20 የመሪዎች ጉባኤ ቀደም ብሎ በባሊ ኢንዶኔዢያ ለመምከር ተስማምተዋል። ንግግሩ ሰዓት እንደተቆረጠለት ያስታወቀው ዋይት ሀውስ ለሁለት ሰዓታት ይቆያል ተብሎ ይጠበቃልም ብሏል።

ዋይት ሀውስ በመሪዎቹ ምን እንደሚጠበቅ ከመናገር መቆጠቡን የዘገበው የአሜሪካው ኤንፒአር፤ ለዚህም ምክንያቱ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው ግልጽ አለመግባባት ነው ብሏል።

የባይደን የብሔራዊ ደህንነት አማካሪ ጃክ ሱሌቫን ወደ ባሊ ለሚጓዙ ጋዜጠኞች እንደተናገሩት ባይደን ሙሉ በሙሉ ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ፕሬዝዳንት ዢን ለመስማት እድሉ አለው ብለዋል።

ሱሌቫን እንዳሉት ዋይት ሀውስ መሪዎቹ ከዚያ ስብሰባ በተሻለ ግንዛቤ እና ይህንን ግንኙነት እና ፉክክርን በኃላፊነት ለመምራት የሚያስችል መንገድ ይዘው እንደሚወጡ ተስፋ አድርገዋል።

ከሆንግ ኮንግ እና ከታይዋን እስከ ደቡብ ቻይና ባህር ድረስ ባሉ በርካታ ጉዳዮች አሜሪካና ቻይና ከቅርብ አመታት ወዲህ ግንኙነታቸው ውጥረቱ ነግሶበታል። የኃያላኑ ሀገራት ግንኙነት በተለይም ባለፉት አስርት ዓመታት ወደ ዝቅተኛው ደረጃ ላይ መውደቁ ይነገርላታልም።

የአሜሪካ ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ናንሲ ፔሎሲ ባለፈው ነሐሴ ቤጂንግ ግዛቴ አካል በምትላት ታይዋን ካደረጉት ጉዞ በኋላ ውጥረቱ ጨምሯል። ጉብኝቱ ቻይናን ያስቆጣ ሲሆን በመቀጠልም አሜሪካ በታይዋን አቅራቢያ ወታደራዊ ልምምድ መጀመሯ ውጥረቱ እንዲያይል አድርጓል ነው የተባለው።

በኢንዶኖዥያው የባይደንና የጂንፒንግ ንግግር ቀዳሚና ዋነኛ አጀንዳ ታይዋን እንደምትሆን ተነግሯል።

ከዚህ ባሻገርም የሩሲያና ዩክሬን ጦርነት ሌላኛው የንግግር አጀንዳ ይሆናል ተብሎ ተጠብቋል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን ማክሰኞ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ጥሩነሽ ዲባባ በክለቧ ልዩ የኒሻን ሽልማት ተበረከተላት

**ብርሃን ፈይሳ**

ታሪካዊው የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን የአትሌቲክስ ክለብ ለጀግናዋ አትሌት ኮማንደር ጥሩነሽ ዲባባ ልዩ የኒሻን ሽልማት አበረከተ። ክለቡ ባለፉት ሶስት ዓመታት ውጤት ላስመዘገቡ አትሌቶቹም የማዕረግና የገንዘብ ሽልማት አበርክቷል።

በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ስፖርት ውጤታማ ከሆኑ ታሪካዊ የስፖርት ክለቦች መካከል አንዱ የሆነው የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን በቀዳሚነት ተጠቃሽ ነው። ኦሊምፒክን ጨምሮ በተለያዩ ዓለም አቀፍ የአትሌቲክስ ውድድሮች ላይ ለአገራቸው በርካታ ሜዳሊያዎችን ማስመዝገብና አገራቸውን ማስጠራት የቻሉ አትሌቶችን አፍርቷል። ከእነዚህ መካከል ረዳት ኮሚሽነር ጀነራል ደራርቱ ቱሉ፣ ፋጡማ ሮባ እና ጥሩነሽ ዲባባ ብቻ 6 የወርቅ ሜዳሊያዎችን በኦሊምፒክ መድረክ መሰብሰብ ችለዋል። ይህንን ተከትሎም ጀግናዋ አትሌት ኮማንደር ጥሩነሽ ዲባባ የልዩ ኒሻን ተሸላሚ ልትሆን ችላለች። ሽልማቱ ከረዳት ኮሚሽነር ጄነራል ደራርቱ ቱሉ ቀጥሎ ለሁለተኛ ጊዜ መሆኑንም ለማወቅ ተችሏል።

አትሌቷ አገሯን በወከለችባቸው አራት ኦሊምፒኮች (አቴንስ፣ ቤጂንግ፣ ለንደን እና ሪዮ ኦሊምፒኮች) 3 የወርቅ እና 3 የነሃስ ሜዳሊያዎችን አግኝታለች። ይህም በኢትዮጵያ የኦሊምፒክ ተሳትፎ ታሪክ በመድረኩ እንድትሆን አስችሏታል። ከረጅም ርቀት የምንጊዜም ስኬታማ የዓለም አትሌቶች አንዷ የሆነችው ጥሩነሽ ዲባባ ከኦሊምፒክ ባሻገር በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናም 5 የወርቅ እና 1 የነሃስ ሜዳሊያዎችን እንዲሁም በዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮና እና የአፍሪካ ቻምፒዮናዎች 6 የወርቅና 3 የብር ሜዳሊያዎችን በማጥለቅ በአትሌቲክስ ሕይወት ወደር የሌለው ስኬት በመጎናፀፍ የአገሯን ባንዲራ አውለብልባለች። ይህንን ተከትሎም ክለቧ የክብር ሽልማቱን ሊያበረክትላት ችሏል። አትሌቷም በተሰጣት ሽልማት መደሰቷን ገልጻለች። በማረሚያ ቤት ስፖርት ክለብ ትንሽ ልጅ ሆና ተቀጥራ አሁን ለደረሰችበት ደረጃ መብቃቷንም ነው ጥሩነሽ ያመላከተችው። ‹‹የማረሚያ ቤት ስፖርት ክለብ ወጣት አትሌቶች ጠንክረው እንዲሰሩ፣ እንዲበረታቱና የተሻለ ደረጃ እንዲደርሱ ያደርጋል›› ያለችው አትሌቷ በተለያዩ የውድድር መስኮች ሁለት ወይንም ሶስት ወርቅ ከተገኘ አንዱ በማረሚያ ቤት አትሌት መሆኑን መግለጻንም ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የተገኘው መረጃ አመላክቷል።



የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ክለብ ለ34 ስፖርተኞች ከረዳት ሳጅን እስከ ኮማንደር ድረስ የማዕረግ ዕድገት ሰጥቷል፣

በአራት የስፖርት ዓይነቶች አትሌቶችን የሚያሰለጥነው የፌደራል ማረሚያ ቤቶች ስፖርት ክለብ በየውድድር መስኩ ለብሄራዊ ቡድን ተመራጭ የሆኑ ስፖርተኞችን ያፈራና እያፈራም ያለ ስመጥር ክለብ ነው። ባለፉት ሶስት ዓመታትም 26 የወርቅ፣ 31 የብር እና 38 የነሃስ በድምሩ 95 ሜዳሊያዎችን በተጨማሪም 8 ዋንጫዎችን እና 47 ዲፕሎማዎችን በዓለም አቀፍ እና በአገር ውስጥ ውድድሮች ማግኘቱንም በሽልማት አሰጣጥ ስነ ስርዓቱ ላይ ተገልጻል። ይህ ውጤት የተመዘገበውም በ78 የክለቡ አትሌቶች ሲሆን፤ ለ34 ስፖርተኞች ከረዳት ሳጅን እስከ ኮማንደር ድረስ የማዕረግ ዕድገት ሲሰጥ፤ ለ19 ስፖርተኞች የገንዘብ እና ለ13 ስፖርተኞች ደግሞ የእርከን ጭማሪና የገንዘብ ሽልማት ተሰጥቷል።

የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን በቅርቡ በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ስፖርት ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ ለሚገኙት የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ደራርቱ ቱሉ እንዲሁም አሰልጣኝ ሁሴን ሽቦ የረዳት ኮሚሽነር ጄነራል ማዕረግ መስጠቱ የሚታወስ ነው። ክለቡ በዚህ ወቅት በአትሌቲክስ ስፖርት በሁለቱም ጾታዎች 105 አትሌቶችን እያሰለጠነ የሚገኝ ሲሆን፤ በኦሬጎኑ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ኢትዮጵያ ካስመዘገበቻቸው አራት የወርቅ ሜዳሊያዎች መካከል ሁለቱ የተገኙት በዚሁ ክለብ አትሌቶች እንደነበር ይታወሳል።

Ethiopian Cooperative Commission (FCC)

## ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር

በየሳምንቱ የሚታተም

# የዳሞት ሁለ-ገብ ኅብረት ስራ ማህበራት ዩኒዬን ከየት ወዴት

**ዳኛቸው ቀደማቸው**

> ዩኒየኑ ወደ ኢንቨስትመንትና አግሮ ፕሮሰሲንግ ስራዎች ውስጥ ለመግባት በቡሬ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ውስጥ ገብቶ የበቆሎ ምርትን ለማቀነባበር የ450 ሚሊዮን ብር ፕሮጀክት ቀርፆ የአዋጭነት ጥናት ተጠንቶና በሙያተኞች ተገምግሞ የቅድመ ዝግጅትና የገንዘብ ማሳባሰብ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ

የህብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች ተመሣሣይ ዓላማ ባላቸው መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት በኅብረት ሥራ አዋጅ በተወሰነው አነስተኛው የአባላት መነሻ ቁጥር መሠረት ከመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት በላይ የሆነ የማምረት፣ አገልግሎት የመስጠት ወይም ሁለቱንም የማከናወን ተግባር ያላቸው ናቸው። ከነዚህ ውስጥም አንዱ በአማራ ክልል ምእራብ ጎጃም ዞን ቡሬ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚገኘው ዳሞት ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን ነው።

አቶ መዝገቡ መኮንን የዳሞት ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን ስራ አስኪያጅ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፤ ዩኒየኑ ህዳር 21 ቀን 1993 ዓ.ም የተቋቋመ ሲሆን በሁለት ወረዳዎችና በስድስት መሰረታዊ ማህበራት 185 ሺህ መነሻ ካፒታል ስራ ጀምሯል። በጊዜው ዩኒየኑ እንቅስቃሴ የጀመረውም ስምንት ሺ የሚሆኑ አባል አርሶ አደሮችን ይዞና ሶስት ሰራተኞችን ቀጥሮ ነበር። የዩኒየኑ ምስረታ መነሻ ምክንያትም የአርሶ አደሮች የግብርና ግብአት እጥረትና የሸቀጣ ሸቀጥ እቃዎች ተደራሽ ያለመሆን ነበር።

እስካሁን ባለው የሃያ ዓመታት ጉዞውም ካፒታሉ ወደ 229 ሚሊዮን ብር ማድረስ ችሏል። በርካታ ውጣ ውረዶችንም አልፏል። ቀጥሮ የሚያሰራቸው ሰራተኞች ቁጥርም 114 ሰራተኞች ናቸው ። አገልግሎቶቹንም በሰባት የገጠር ወረዳዎችና በሶስት ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ ይሰጣል። በውስጡም 84 የሚደርሱ መሰረታዊ ማህበራትንና በነዚሁ መሰረታዊ ማህበራት ውስጥ የታቀፉ 180 ሺ በላይ አባወራና እማወራዎችን ይዟል።

የስራ አድማሱንም ሲቋቋም ከነበረበት እየጨመረ በመሄድ ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ለአባል አርሶ አደሮቹና ለሌላውም የአካባቢው ማህበረሰብ ተደራሽ ማድረግ ችሏል። አባላት ያመረቷቸውን ምርቶችንም ገበያ አፈላልጎ በሚፈለገው መጠንና የጥራት ደረጃ ለተጠቃሚው ያቀርባል። ምርትና ምርታማነትን ለመጨመርም የሜካናይዜሽን አገልግሎት ለአባል አርሶ አደሮች ይሰጣል። 12 የሚሆኑ ማረሻ ትራክተሮችና ሁለት ኮምባይነሮችም አሉት። በነዚህ ማሽኖችም ለአባል አርሶ አደሮች እህሎችን የማጨድና የመውቃት እንዲሁም የእርሻ መሬቶችን የማረስና የመከስከስ አገልግሎቶችን ያከናውናል።

በሌላ በኩል ደግሞ በዛው በቡሬ ከተማ በሚገኘው የአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫው አነስተኛ የእርሻ መሳሪያዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለአባል አርሶ አደሮችና ለአካባቢው ማህበረሰብ ይሸጣል። ኬሚካሎችን፣ የአትክልትና የደን ዘሮችን፣ የድህረ ምርት ማሸጊያ ከረጢቶችንና የእንስሳት መድሃኒቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለአባላቱና ለአካባቢው ማህበረሰብ ያቀርባል። በ2005 ዓ.ም በዘጠኝ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ያቋቋመው የስንዴ ዱቄት ፋብሪካም በቀን 420 ኩንታል የመፍጨት አቅም ያለው ሲሆን ስንዴውን ሙሉ በሙሉ ከአባል አርሶ አደሮች ይረከባል። በአካባቢው በአነስተኛና ጥቃቅን ተደራጅተው ዳቦ በመጋገርና በመሸጥ ለሚተዳደሩ ሰዎች የዱቄት ግብአት በማቅረብም የበኩሉን አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል።

ዩኒየኑ የትምህርትና ስልጠና አገልግሎት ለአባላቱ የሚሰጥ ሲሆን ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ አንፃር ግንዛቤና እውቀት እንዲኖራቸው አግዟል። በተያያዥነትም በዩኒየኑ ስር ያሉ ማህበራትና ህብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን አስችሏል።

ከዚህ በዘለለ ዩኒየኑ በየአመቱ ከሚያገኘው ትርፍ የማህበራዊ አገልግሎቶችንም ለአካባቢው ማህበረሰብ ይሰጣል። እስካሁን ባለው ሂደትም በአንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ብር ደጋ ዳሞት ላይ አንድ ብሎክ ትምህርት ቤት ገንብቶ አስረክቧል። በተመሳሳይ በደምበጫ ወረዳ 452 ሺ ብር ወጪ አድርጎ የእንስሳት ጤና ኬላ ገንብቷል። በቡሬ ከተማም ዙሪያ ግንባታው እየተከናወነ ለሚገኝ አንድ ትምህርት ቤትም የ300 ሺ ብር ድጋፍ ሰጥቷል። በዛው ቡሬ ከተማ ለሚገኝና እድገት በህብረት ለሚባል ትምህርት ቤትም 70 የተማሪዎች መቀመጫ ወንበሮችን አሰርቶ አስረክቧል። በዚህም ዩኒየኑ ለማህበራዊ አገልግሎት ዘርፍ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ጎልቷል።

ስራ አስኪያጁ እንደሚሉት፤ በአሁኑ ወቅት ዩኒየኑ ወደ ኢንቨስትመንትና አግሮ ፕሮሰሲንግ ስራዎች ውስጥ ለመግባት በቡሬ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ውስጥ ገብቶ የበቆሎ ምርትን ለማቀነባበር የ450 ሚሊዮን ብር ፕሮጀክት ቀርፆ የአዋጭነት ጥናት ተጠንቶና በሙያተኞች ተገምግሞ የቅድመ ዝግጅትና የገንዘብ ማሳባሰብ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ። ለዚህም አብዛኞቹ አባል አርሶ አደሮች እጣ ገዝተው ማቀነባበሪያውን በራስ አቅም እንዲገነቡ ጥረት እየተደረገ ነው። ዩኒየኑ በቆሎን ወደ ማቀነባበር ስራው ሲገባም 50 ከመቶ ያህሉን የበቆሎ ዱቄት፣ 25 ከመቶውን ቅንጬ እንዲሁም ቀሪው 25 ከመቶውን ለውጪ ገበያ የሚሆን ስታርች የማምረት እቅድም ይዟል።

ዩኒየኑ በቀጣይም የጀመራቸውን የግብርና ምርቶች ወደ ውጪ አገር የመላክ ስራዎች የማጠናከርና የማስፋት አቅድ አለው። የግብርና ማሽነሪዎችን ቁጥር በመጨመር ምርቱን የማስፋት ውጥንም ይዟል። ወደ ውጪ አገራት በሚልካቸው የግብርና ምርቶች ከሚገኘው ገቢም ለመንግስት ተገቢውን የውጭ ምንዛሬ የማስገኘት ፍላጎትም አለው።

ህብረት ስራ ማህበራት በትክክል ከተተገበሩ የድህነት መውጫ መንገዶች ከመሆናቸው አኳያም አባል ያልሆነ መላው አርሶ አደር በህብረት ስራ ማህበር አባልነት ውስጥ ገብቶ የራሱን አስተዋፅኦ የሚያበረክትበትን እድል መጠቀም እንደሚኖርበት ዩኒየኑ ይመክራል።

በሃያ አመታት ቆይታው ዩኒየኑ ለዚህ ውጤት ሊበቃ የቻለውም የህብረት ስራ ትክክለኛ አዋጆችን፣ መመሪያዎችንና ደንቦችን በአባላቱ ውስጥ በማስረፅና እነርሱን ይዞ መጓዝ በመቻሉ ነው። የህብረት ስራ እሴቶችን በተከተለ መልኩና አባላቱን ባሳተፈ ሁኔታ ስራዎችን መስራቱ ብሎም እነዚሁ እሴቶች በአባላት ውስጥ እንዲሰርፁ ማድረጉም ለዩኒየኑ ውጤት የራሱን አስተዋፅኦ አበርክቷል።

አድራሻ | የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Federal cooperative Agency | Website: www.fca.gov.et

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ